# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ
# ማስፈጸሚያ መምሪያ (Guideline)

ረቂቅ 1.0

አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ

2013 ዓ.ም

# ትርጉም፣

- **ዓላማ**:-የትኩረት አቅጣጫው ለምን እንዳስፈለገ የሚገልጽ ነው፡፡
- **አድማስ**:-እያንዳንዱ የትኩረት አቅጣጫ በምን ሁኔታዎች ላይ ሊተገበር እና ሊከናወን እንደሚችል ያለውን ትኩረት የሚያሳይ ነው፡፡
- **መስፈርት**:-እያንዳንዱን የትኩረት አቅጣጫዎች በሥራ ላይ ለማዋል ምን ምን ጉዳዮች መከናወን እንዳለባቸው ይገልጻል፤
- **ቁጥጥር**:-አንድ የትኩረት አቅጣጫ መተግበሩን ወይም አለመተግበሩን የሚያሳዩ ምክንያቶችን የሚያትት ነው፡፡
- **የትግበራ መምሪያ**:-የሚመለከታቸው አካላት እንዴት አድርገው በዚህ መምሪያ ውስጥ የተጠቀሱ የትኩረት አቅጣጫዎች በስራ ላይ ማዋል እንደሚችሉ የሚገልጽ ነው፡፡

## ማውጫ


1. መግቢያ .... 4
2. የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ መምሪያ አስፈላጊነት .... 4
3. አድማስ .... 5
4. ዓላማ .... 5
   4.1. ዝርዝር ዓላማዎች .... 5
5. መምሪያውን እንዴት መጠቀም ይቻላል ? .... 6
6. የብሄራዊ ሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ የትኩረት አቅጣጫዎች .... 6
   6.1. የህግና የቁጥጥር ማዕቀፍ .... 6
   6.2. የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና .... 9
   6.3. የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ .... 12
   6.4. የሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት .... 19
   6.5. የዲጂታል ማንነትና ግላዊ መረጃ ጥበቃ .... 20
   6.6. ቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማት ጥበቃ .... 22
   6.7. ሃገር-አቀፍ እና ዓለም-አቀፍ ትብብር .... 25
7. የባለድርሻ አካላት ኃላፊነትና ሚና .... 31
   7.1. ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ .... 31
   7.2. ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ምክር ቤት .... 32
   7.3. የኢትዮ ሰርት (CER²T) .... 32
   7.4. የህግ  አካላት .... 32
   7.5. የግሉ ዘርፍ .... 32
   7.6. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት .... 33
   7.7. ቁልፍ የመሰረተ-ልማት ዘርፎች .... 33
8. ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ የማስፈጸሚያ መርሃ ግብር .... 34

## 1. መግቢያ

ይህ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ መምሪያ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ በብሄራዊ ደረጃ ግልጽና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለመተግበር ያስችላል፡፡ መምሪያው በፖሊሲና ስትራተጂው የተጠቀሱ አንኳር ሰባት የትኩረት አቅጣጫዎች የሚተገበሩበትን መንገዶች በማሳየት የአገሪቱን የሳይበር ደህንነት አቅም በሁሉም ዘርፎች ለማሳደግ ያለመ ነው፡፡

በመሆኑም ፖሊሲና ስትራቴጂው በስኬት እንዲተገበር እና ለትግበራው ተግዳሮት የሚሆኑ ውጫዊ ሁኔታዎች በማስወገድ በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ተስማሚ የሆኑ የሀብት ምንጮች በማቀናጀት፣ ተቀባይነት ያለው የመንስኤና ውጤት ንድፈ-ሀሳብ በማስቀመጥ፣ በመንስኤና ውጤት መካከል ቀጥተኛ የሆነ ትስስር እንዲኖር በማድረግ፣ አንድ ዋና እና ብቸኛ ለሆነ ተግባሪ ተቋም ኃላፊነት በመስጠት፣ በሚከናወኑ ግቦች ዙሪያ መግባባትና ስምምነቶች በመፍጠር ሊፈጸሙ ስለሚገባቸው ተግባራት ዝርዝር የሆነ ገለጻ ማስቀመጥ፣ ግልጽ የሆነ ተግባቦትና ቅንጅት እንደቁልፍ ተሞክሮ አድርጎ በመውሰድ አስፈላጊ ነጥቦችን በተፈለገው ጊዜና ቦታ ታሳቢ በማድረግ የተቀረጸ ነው፡፡

በአጠቃላይ ይህ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ መተግበሪያ መምሪያ የተቀናጀውና የተዘጋጀው ከላይ የተጠቀሱትን የጽንሰ-ሀሳብ ማዕቀፎች ግምት ውስጥ አስገብቶ በመሆኑ በኢትዮጵያ በሳይበር ደህንነት ዘርፍ ለማሳካት የሚፈለገውን መሻሻል በማምጣት በኩል ጉልህ ሚና ይኖረዋል፡፡

## 2. የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ መምሪያ አስፈላጊነት

አሁን ያለው አለም አቀፍ የሳይበር ደህንነት ነባራዊ ሁኔታ እና በሃገራችን የኮሙኒኬሽን እና ኢንፎርሜሽን ስርዓት እያደገ መምጣት መልካም አጋጣሚዎች እንዳሉት ሁሉ ተግዳሮቶችም ይስተዋላሉ፡፡ እንዲሁም ብሔራዊ ደህንነት ላይ የተጋረጠ የሳይበር ስጋትና ተጋላጭነት እንዳለ ሁሉ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል የሕዝብ ሰላምና ደህንነት፣ የዜጎች መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን መጠበቅ ተገቢ ነው፡፡ ይህም ሃገራት የሚገጥሟቸውን እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቋቋም የራሳቸውን የሳይበር ደህንነት ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ማዕቀፎች ያወጣሉ፡፡

የዚህ ማስፈጸሚያ መምሪያ መኖር አሁን ላለው የሃገሪቱ የሳይበር ደህንነት ወቅታዊ እና መፃኢ ዕድሎች ትክክለኛ አቅጣጫ እና ስትራቴጂ ለማመላከት፣ ፖሊሲ እና ስትራቴጂውን በአግባቡ ለመምራት፣ የመንግስት እና የግል አጋርነት ትብብር እንዲኖር ለማድረግ፣ እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ፖሊሲውን ለማስፈጸም በሃገር ዓቀፍ ብሎም በአለም ዓቀፍ ደረጃ የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ አስፈላጊ ነው።

ስለሆነም ይህ የማስፈጸሚያ መምሪያ የሳይበር ደህንነት ዓላማዎች፣ግቦች፣መርህዎችና አጠቃላይ ይዘት መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን ለተግባራዊነቱ የዜጎችን፣ የመንግስትን፣ የግል ተቋማትን እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በማቀናጀት የሳይበር ደህንነትን በማረጋገጥ ብሔራዊ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ ያስችላል።

## 3. አድማስ

ይህ መምሪያ የመንግስትና የግል ተቋማትን ጨምሮ በሃገሪቱ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቀላሉ እንዴት ***ብሄራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂን*** ወደ ተግባር ሊያወርዱት እንደሚችሉ የሚያሳይ ጠቋሚና ተግባራዊ ምክረ-ሀሳቦችን የያዘ ነው።

## 4. ዓላማ

የዚህ መምሪያ ዓላማ የብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ የትኩረት አቅጣጫዎችን እና ግቦችን በአግባቡ በማመላከት የፖሊሲና ስትራቴጂውን ተፈፃሚነት ዕውን ለማድረግ፤እንዲሁም የፖሊሲና ስትራቴጂው አተገባበር ግልጽና ሁሉን አሳታፊ እንዲሆን በማድረግ የሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማድረግ ነው።

### 4.1. ዝርዝር ዓላማዎች

- የፖሊሲና ስትራቴጂ የትኩረት አቅጣጫዎችን በዝርዝር ለማመላከት፤
- ለመንግስት እና ለግል ተቋማት ፖሊሲና ስትራቴጂውን ለመተግበር የሚረዱ ጠቃሚ ምክረ-ሀሳቦችን ለማመላከት፤
- ኢትዮጵያ ከሌሎች ሃገር-አቀፍ እና ዓለም-አቀፍ ተቋማት፤ እንዲሁም ከተለያዩ ሃገራት ጋር አጋርነት እና ትብብር በመፍጠር እንዴት የሳይበር ደህንነቷን ማሳደግ እንደምትችል አቅጣጫ ለማሳየት፤
- ግልጽና ሁሉን ዓቀፍ በሆነ ሁኔታ የባለድርሻ እና ተባባሪ አካላት ሚና በአግባቡ በዝርዝር በማስቀመጥ ሁሉም አካላት የየራሳቸውን ድርሻ እና ሚና በመለየት ለተግባራዊነቱ የበኩላቸውን እንዲወጡ ለማስቻል፤

## 5. መምሪያውን እንዴት መጠቀም ይቻላል ?

- ብሄራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂን በሚገባ መረዳት፤
- ፖሊሲና ስትራቴጂው ከትግበራ መምሪያው ጋር በማነጻጸር መረዳት፤
- ከእያንዳንዱ የትኩረት አቅጣጫ ትይዩ የተቀመጠውን የትግበራ መምሪያ መረዳት፤
- ዓላማዎቹ በትግበራ መምሪያው ስር ከተቀመጡትን ነጥቦች ጋር ያለውን ዝምድና መረዳት፤
- በትግበራ መምሪያው ስር ያሉትን ነጥቦች ወደ ተግባር ለማውረድ መትጋት፤

## 6. የብሄራዊ ሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ የትኩረት አቅጣጫዎች

### 6.1. የህግና የቁጥጥር ማዕቀፍ

#### 6.1.1. መግቢያ

የሃገራችንን የሳይበር ደህንነት የሚያስጠብቁ ሕግጋት እና የቁጥጥር ማዕቀፎች ማልማቱ፣ ማጽደቁ እና ተፈጻሚ ማድረጉ የሳይበር ተጋላጭነትና ስጋት ከመቀነስ ባሻገር የሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነቶቻቸውንና ግዴታዎቻቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም የሃገሪቱን ብሄራዊ የሳይበር-ምህዳር እና ቁልፍ መሰረተ-ልማቶችን ደህንነት ለማስጠበቅ፣ ከጥቃት ለመከላከል፣ ጥቃት ሲፈጸም ምላሽ ለመስጠት፣ ለሕግ ለማቅረብ እና የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ በማህበረሰቡ ዘንድ እንዲሰርጽ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የሚከተሉት ግቦች፣ መስፈርቶች፣ የቁጥጥርና የትግበራ መምሪያዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

#### 6.1.2. ግቦች

1. የሳይበር ደህንነት ስጋቶችንና ተጋላጭነቶችን ለመቀነስ፤ ጥቃቶችን ለመከላከል እና ለመቋቋም የሚያግዙ፤ እንዲሁም ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸውቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ህጎችእና ስታንዳርዶች ጋር ተጣጣሚነት ያላቸው የሳይበር ደህንነት ሕግጋት እና ቁጥጥር ማዕቀፎችን ማውጣት፤ በቀጣይነትም ማሻሻል፤

2. የሳይበር ወንጀል፣ ሳይበር ሽብርተኝነት፣ የሳይበር ስለላ እና መሰል ጥቃቶች ለመከላከል የሚያስችል የህግ አካላትን አቅም መገንባት፤
3. በሀገር ውስጥ የሚመረቱና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የሳይበር ደህንነት ምርቶችና አገልግሎቶች፤ እንዲሁም ቁልፍ የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎች ሀገራዊ የሳይበር

ደህንነት ፍላጎትን ያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፤

4. ማህበረሰቡ በሀገሪቱ የሳይበር ደህንነት አቅሞች ዙሪያ ያለውን ዓመኔታ ለማሳደግ በኢንፎርሜሽን አሰባሰብ፣ ትንተና፣ ስርጭት፣ አጠቃቀም፣ ክምችት እና አወጋገድ ዙሪያ ደረጃቸውን የጠበቁ የህግና ቁጥጥር ማዕቀፎችን መዘርጋት፤

### 6.1.3. አድማስ

ይህ የትኩረት አቅጣጫ በኢትዮጵያ የሳይበር ደህንነት የህግና ቁጥጥር ማዕቀፎችን በማልማት፣ አቅም በመገንባት እና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ዙሪያ የሚያተኩር ነው።

### 6.1.4. መስፈርት

የሃገሪቱን የሳይበር ደህንነትን በተፈለገው መጠን ለማሳደግ የሚመለከታቸው አካላት እንደአስፈላጊነቱ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ወደ ተግባር ለማውረድ የሚያችሉ ህጎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ስታንዳርዶች፣ መመሪያዎች እና ሌሎች የቁጥጥር ማዕቀፎችን በመውጣት ስራ ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል።

### 6.1.5. ቁጥጥር

ይህ የትኩረት አቅጣጫ በትክክል ተተግብሯል የሚባለው የሃገሪቱ የሳይበር ደህንነት የህግና የቁጥጥር የትኩረት አቅጣጫ ክፍተት በጥናት እየተለየ ሲለማና ሲተገበር ነው።

### 6.1.6. የትግበራ መምሪያ

- ተጋላጭነቶችን በማግኘት መፍትሄ ለመስጠት ይቻል ዘንድ ህጋዊና የቁጥጥር እርምጃዎችን አሁን ያለውን የመንግስት/የህዝብ ዘርፍ፣ የግሉ-ዘርፍ እና የኮምፒውተር ኢንፎርሜሽን ስርዓት ተጠቃሚዎችን ህጋዊ ግዴታዎችና ኃላፊነቶችን ባካተተ መልኩ ግምገማ ማድረግ፤
- ኢትዮጲያ የፈረመቻቸው ከሳይበር ጋር የተያያዙ የዓለም-አቀፍ ህግ ስምምነቶች እና ግዴታዎች፣ እንዲሁም በተለያዩ ዓለም-አቀፍና አህጉር-አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ አባል ከመሆኗ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ኃላፊነቶችና ግዴታዎችን ለመወጣት እንዲቻል የፖሊሲና ህጋዊ ማእቀፎችን ማሻሻል፤
- ብሄራዊ የሳይበር ህግጋት ተያያዥነት ባለው አጠቃላይ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለሳይበር ስጋቶች መልስ እንዳይሰጥ የሚያደርጉትን ክፍተቶች መለየት፣ እነዚህ ክፍተቶች ለመመከት አስፈላጊ የሆኑ ህጋዊ እርምጃዎችን ማጎልበት

እንዲሁም እነዚህን የቀረቡ ሀሳቦች ከሌሎች ህጋዊ የሆኑ ግለሰባዊና ማህበረሰባዊ ባለድርሻ አካላት ጥቅሞች ጋር በጥንቃቄ ሚዛናቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ማድረግ፤

- አስፈላጊ የሆኑ ህግጋትን ከሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማስማማት መጠቀም እንዲሁም ዓለም-አቀፍ ስምምነቶችን መፈረም፤
- ልዩ ስልጠና የወሰዱ አባላትን የያዙ ብሄራዊ የሳይበር-ወንጀል መምሪያዎችን/units/ (ህግ አስፈጻሚና የህግ አውጪ ባለስልጣናትን የያዘ) ማቋቋም፤
- ለፀጥታ አካላት ቀጣይነት ያለውና ልዩ የሆነ ስልጠና መሰጠቱን ማረጋገጥ (ለምሳሌ፡- ዲጂታል ፎሬንሲክን በተመለከተ)፤
- ፖሊሶች እና ዳኞች ተጣጣሚ በሆነ መልኩ መረጃን ማስቀመጥ/record-keeping/ የሚያስችሏቸውን ደንቦች እንዲሁም የኮምፒውተር ወንጀሎችን ስነ-ግምታዊ/statistical ትንተና ለማድረግ የሚያስችሉ ተገቢ መሳሪያዎችን መፍጠር፤
- በተለያዩ ባለድርሻ አካላት መካከል ትብብርን ለማጎልበት መድረኮችን ማዘጋጀት (ለምሳሌ፡- የኮምፒውተር ድንገተኛ አደጋ መልስ ሰጪ ቡድኖች/CERTs እና የመረጃ አካላት)፤
- ኢንዱስትሪዎች በኮምፒወተርና ኮምፒውተር ስርዓቶች ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን ለመከላከል ቀጥተኛ እርምጃ እንዲወስዱ ማበረታታት፤
- አዳዲስ ዲጂታል ፎረንሲክ ስልቶችን በተመለከተ መሪ ከሆኑ የትምህርት እንዲሁም ከምርምርና ልማት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ፤
- ከሳይበር ወንጀሎች ጋር ዝምድና ያላቸውን ጉዳዮች በፍጥነት ለመለየትና መልስ ለመስጠት የመንግስትና የግል አጋርነቶችን፤ መመስረትና ማጠናከር፤
- የሳይበር ደህንነት ችግሮች ከሞላ-ጎደል ሊሸፍኑ የሚችሉ የሚከተሉትን የህግ ዓይነቶች አጽድቆ ስራ ላይ ማዋል፣
  1. የግላዊ ሕይወት እና የግል ዳታ ማስኬጃ ህግ/Privacy and Personal Data Processing Law/፡- የሳይበር-ክስተት ኩነት በሚኖርበት ጊዜ ኦፕሬሽናል የኢንፎሜሽን መጋራት መርሆችን ጨምሮ፤
  2. የቴሌኮሙኒኬሽኖች ህግ/Telecommunications Law/፡- የኮምፒውተር ስርዓት መሰረተ-ልማቶችና የአገልግሎት ቀጣይነትን ለማጋገጥ የሚረዱ የዳታ ኮሙኒኬሽኖች አገልግሎት ሰጪዎችን፤ የኮሙኒኬሽን ኔትዎርኮች ላይ የደህንነት ወይም የተአማኒነት ስጋት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ አገልግሎት ሰጪዎች ጣልቃ የሚገቡባቸውን ዘዴዎች ጨምሮ፤

3. የሳይበር ወንጀል እና የሳይበር ወንጀለኛ ስነ-ስርዓት ህግ፡-
4. ቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማት ጥበቃ እና የቀውስ አስተዳደር ህግ/Critical Information Infrastructure Protection and Crisis Management Law/፡-

## 6.2. የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና

### 6.2.1. መግቢያ

የሳይበር ደህንነት ስጋቶችና ተጋላጭነቶች በማህበረሰቡ ላይ የሚያሳርፉትን ተጽእኖ በተመለከተ የማህበረሰቡን ንቃተ-ህሊና ማሳደጉ እጅግ ጠቃሚ እየሆነ መጥቷል፡፡ ስለሆነም በሀገሪቱ በሳይበር ደህንነት አካላት ዘንድ የሳይበር ስጋቶችንና ተጋላጭነቶችን ለመቀነስ የህብረተሰቡ ንቃተ-ህሊና ከፍ በማድረግ፤ የመረጃ ዋጋና የሳይበር ደህንነት ጥቃት አስመልክቶ በእውቀት ላይ የተመሰረተ የመረጃ ልውውጥ ባህል እንዲጎለብት፤ እንዲሁም የአመለካከትና የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ እና እንዲዳብር ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፡፡

### 6.2.2. ግቦች

1. የመንግስት ተቋማት፣ የግል ተቋማትና ዜጎች በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ያላቸውን እውቀትና አመለካከት ማዳበር፤
2. ከጥንቃቄ ጉድለትና ካለማወቅ የሚደርሱ የሳይበር ጥቃቶች፣ ስጋቶች እና ተጋላጭነቶችን መቀነስ፣
3. የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶችና ስጋቶች ለመቀነስ፤ እንዲሁም ጥቃቶች ለመከላከል የሚያስችል የዜጎች ንቃተ-ህሊና ማሳደግ እና ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ባህል መፍጠር፤

### 6.2.3. አድማስ

ይህ የትኩረት አቅጣጫ የሚያተኩረው የማህበረሰቡን የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ከፍ በማድረግ ዙሪያ ነው፡፡

### 6.2.4. መስፈርት

የማህረሰቡን የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ለማዳበር ቀጣይነት ያላቸው መድረኮች፣ ሴሚናሮች፣ ኮንፈረንሶች፣ ስልጠናዎች፣ መርሀ-ግብሮች፣የሚዲያ ፕሮግራሞችና ሌሎችም በሃገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ በሚካሄዱትም ላይ ተሳትፎ መደረግ ይኖርበታል፡፡

### 6.2.5. ቁጥጥር

ይህ የትኩረት አቅጣጫ በአግባቡ መተግበሩ የሚረጋገጠው የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊናን ለማሳደግ ዘርፈ-ብዙ እንቅስቃሴዎች በሁሉም ባለድርሻ አካላት ሲደረግ ነው፡፡

### 6.2.6. የትግበራ መምሪያ

- በሁሉም ደረጃዎች ላሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ተገቢ የሆነ የመረጃ አጠቃቀም አቅም የመጨመር አስፈላጊነት ግምት ውስጥ በማስገባት ለንቃተ-ህሊና እርምጃዎች ተገቢ የሆኑ አድማጮች እና/ወይም ተመልካቾች መለየት፤
- በሃገሪቱ ውስጥ የሳይበር ደህንነት ባህልን ማጠናከርን እና ለህዝብ ይፋ የሆኑትን እና/ወይም ኢላማ የተደረጉ የመረጃ ቁሶችን ጨምሮ ከሳይበር ደህንነት ጋር በቀጥታ የተገናኙ ወይም ሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ የተለያዩ የሙያ መስኮች ላይ የተሰማሩ ሙያተኞችን የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ማሻሻል፣
- በኦንላይን የንቃተ-ህሊና እና መማሪያ ክባቢና መሳሪያዎችን፣ የሳይበር ዕውቀት ለማሳደግ የሚረዱ መሰረታዊ የትምህርት መርሀ-ግብሮችን፤ እንዲሁም ከዚህ ከፍ ባለ ደረጃ የንቃተ-ህሊና እርምጃዎች ተስማሚነትና ውጤታማነት ለመዳሰስ ጠቃሚ ሚና ያለው በመረጃና ኔትዎርክ ደህንነት፣ ቴክኒካዊና/ኦፐሬሽናል ገጽታዎችን፣ ስትራቴጂያዊና ፖለቲካዊ ውሳኔ የመስጠት ቅደም-ተከተሎችን ወይም ሁለቱንም ያካተተ የሳይበር መከላከል ልምምዶች ልዩ የሆነ የስልጠና ካሪኩለምና መርሀ-ግብሮችን የያዙ እንቅስቃሴዎች ማድረግ፤

  - ለንቃተ-ህሊና ማጎልበት ዘመቻ ኢላማ ተደርገው የተመረጡትን አድማጮች እና/ወይም ተመልካቾች በሚገባ መለየት (ለምሳሌ፡- ዜጎች፣ የኮምፒወተር ምርቶች ተጠቃሚዎች/end-users/፤
  - ለተለያዩ የሳይበር ተጠቃሚ ማህበረሰብ ክፍሎች ንቃተ ህሊና ማሳደጊያ ዘዴዎችን ማልማት፤
  - ኢላማ የተደረጉትን አድማጮች እና/ወይም ተመልካቾች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የተለመዱ ባህሪያዊ ችግሮችን ወይም ኢላማ የተደረጉት አድማጮች እና/ወይም ተመልካቾች ሊያውቋቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መለየት፤
  - የብሄራዊ መረጃ ደህንነት ልዩ መለያ/unique/ መፍጠር፡- የስትራቴጂ ዓላማዎችን የሚደግፉ ግልጽ የሆነ የመረጃ ደህንነት ርዕሶችን መምረጥ ከዚያም በሃገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም-አቀፍና በአካባቢያዊ ኩነቶች ላይ

ተገቢ የሆኑ የኮሙኒኬሽን መስመሮችን/channels/ በመጠቀም ማደረጀትና ማስተዋወቅ፤

- የሳይበር ደህንነት ንቃተ ሂሊና ባህል ግንባታውን ለማጠናከር እንዲቻል በየጊዜው የተለያዩ ጉዳዮችን የያዘ በመንግስት፣ ወይም ከግሉ ዘርፍ ጋር በአጋርነት ብሄራዊ የሳይበር ደህንነት ወር፣ ሳምንትና ቀን ማዘጋጀት፤
- ደህንነቱ በተጠበቀ መንግስታዊ ድረ-ገጽ ከመረጃ ደህንነት ጋር ዝምድና ባላቸው ቁሶች(ለምሳሌ፡- በድረ-ገጽ ላይ የሚደረጉ ሴሚናሮች/webinars/፣ ትምህርታዊ ዲስኩሮች/lectures/ እና የሚቀርቡ ትምህርቶች ማዳበር፤ የተጠቀሱትን ቁሶች ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎም፤
- ተገቢ የሆኑ ዓለም-አቀፍ ማነቃቂያ ዘመቻዎች ላይ መሳተፍ ወዘተ፤

## 6.3. የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ

### 6.3.1. መግቢያ

በሀገራችን ከሳይበር ደህንነት ጋር በተያያዘ በቂ የሆነ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና ጠንካራ የሳይበር ደህንነት የአሰራር ስርዓቶችና ተቋማዊ መዋቅሮች ባለመኖራቸው ምክንያት የሳይበር ደህንነት አቅም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲሆን አስተዋጽኦ አድርጓል። በመሆኑም ጠንካራ የሆነ የሳይበር ደህንነት አቅም መገንባት መቻል ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ዕድገት እና ለውጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ስለሆነ መንግስት በህብረተሰቡ ዘንድ ጠንካራ የሳይበር ደህንነት ባህል ለመገንባት፤ የትምህርት እና ስልጠና ፕሮግራሞች ለማስፋፋት፤ ተቋማዊ/ መዋቅራዊ አቅሞች እና የአሰራር ስርዓቶች ለመገንባት በሃገር ደረጃ የማይበገር እና ተጣጣፊ የሆነ የሳይበር ደህንነት አቅም መገንባት ተገቢ ነው።

### 6.3.2. ግቦች

1. የሳይበር ደህንነት ስጋት፣ ተጋላጭነት እና ጥቃት ለመለየት፣ ለመዳሰስ እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ተቋማዊ መዋቅሮችንና አቅሞችን መገንባት፤
2. የመንግስት፣ የግል እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሳይበር ደህንነት አቅማቸውን ማጠናከር፤
3. በሀገር ደረጃ ብቃት ያላቸው የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችን መፍጠር፤

### 6.3.3. አድማስ

ይህ የትኩረት አቅጣጫ አድማስ የሚያተኩረው አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ የሃገሪቱን ሁለንተናዊ የሳይበር ደህንነት አቅም በመገንባት ላይ ነው።

### 6.3.4. መስፈርት

ይህ ትኩረት አቅጣጫ ግቦቹን እንዲያሳካ የሚከተሉት መደረግ አለባቸው፦

1) በሃገሪቱ ከሳይበር ደህንነት ጋር የተያያዙ ስልጠናዎችና የትምህርት ፕሮግራሞች ማጠናከር፤
2) ለክስተቶች ጠንካራ የሆነ መልስ የሚሰጥ አቅም መዘርጋት፤
3) ስትራቴጂዎችን ለማልማት፣ ለመፈጸምና ለመገምገም ብሄራዊ የስጋት ዳሰሳ አካሄድን መከተል፤
4) ስትራቴጂዎቹ እንዲሳኩ ግልጽ የሆነ የሳይበር አመራርና አስተዳደር መዋቅር መዘርጋት፤

5) ከጥቃት ቶሎ ማገገም/resilience/ የሚያስችል የሳይበር ደህንነት ልምምዶችን ማጎልበትና ማደራጀት፤

6) ተቋማት ሊከተሏቸው የሚገቡ ዝቅተኛ የደህንነት መስፈርቶችን/baseline security requirements/ ማልማት፤

### 6.3.5. ቁጥጥር

ይህ የትኩረት አቅጣጫ ዓላማዎቹን አሳክቷል የሚባለው የሃገሪቱን የሳይበር ደህንነት አቅም ለማሳደግ የሚረዱ የትምህርት፣ የስልጠና፣ የልምምድ፣ የምርምርና ልማት ተግባራን በማከናወን በዘርፉ ጠንካራ አቅም ሲገነባ ነው።

### 6.3.6. የትግበራ መምሪያ

#### *6.3.6.1. ስልጠናዎችን እና ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን ማጠናከር*

- ብሄራዊ የመረጃ ደህንነት ስልጠና እና ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን መጀመር፤
- በሁሉም የኢንዱስትሪ ዘርፎች ላሉ ቁልፍ የስራ ቦታዎች ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ክህሎት ያላቸው እንዲሆኑ የደህንነት እውቅና/accreditation/ እና የምስክር ወረቀት/certification/ መስጠት፤
- የመረጃ ደህንነት ኃላፊነት ለመውሰድ የሚረዱ ሚናዎች እና ተገቢ የሆኑ የትምህርት ዱራዎችን ዝርዝር ማዘጋጀት፤
- በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ላሉ በኮምፒውተር ሳይንስም ሆነ በሌሎች የትምህርት መስኮች ውስጥ የሳይበር ደህንነት ትምህርት ካሪኩለም መንደፍና መተግበር፤

#### *6.3.6.2. ለክስተቶች መልስ መስጠት የሚያስችል አቅም መፍጠር*

ብሔራዊ የሳይበር ድንገተኛ ዝግጁነትና ምላሽ ሰጪ ቡድኖች /CERTs/ የክስተት አስተዳደር በብሄራዊ ደረጃ ከተገቢ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። እንዲሁም በሌሎች ሃገራት ከሚገኙ መሰል ተቋማት ጋር የማቀናጀቱን ኃላፊነት ይሸከማሉ፡ ፡ በተጨማሪ ተግባራቶቻቸው በተፈለገው መልክ እንዲሳካ የሳይበር ድንገተኛ ዝግጁነትና ምላሽ ሰጪ ቡድኖች/CERTs/ በሚከተሉት ምድቦች ላይ በቂ የሆኑ አቅሞች እንዲኖራቸው ስልጣን መስጠቱ አስፈላጊ ነው፡-

- **ለቡድኖቹ**(/CERTs/ )**ድርሻና ኃላፊነትን መስጠት፡-** በሚመለከተው የመንግስት አካል ለቡድኑ መሪዎችና ባለሙያዎች ሚናዎችና ኃላፊነቶች በግልጽ ለይቶ መስጠት፤

- **የአገልግሎት ዶሴ**/Service portfolio/፡- ይህ የሚመለከተው አንድ ቡድን ለመንግስት የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ወይም ለራሱ ውስጣዊ ስራ የሚጠቀማቸውን አገልግሎቶች የሚያካትት ነው፤
- **ኦፕሬሽናል አቅሞች**/Operational capabilities/፡- ይህ ቡድኑ ሊያሟላቸው የሚገቡ ቴክኒካዊና ኦፕሬሽናል መስፈርቶችን የሚመለከቱ ናቸው፤
- **የትብብር አቅሞች**/Cooperation capabilities/፡- ከላይ ባሉት ምድቦች ያልተነኩትን መረጃ መጋራትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚያቅፉ መስፈርቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ፖሊሲ አውጪዎች፣ ወታደራዊ አካላት፣ ህግ አውጪዎች፣ የቁልፍ ኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማት አንቀሳቃሽ/operators፣ ህግ አስፈጻሚ ባለስልጣናቶችን፤

### 6.3.6.2.1. የትግበራ መምሪያ

- የሳይበር ድንገተኛ ዝግጁነትና ምላሽ ሰጪ ቡድኖች የውክልና ስራቸውን መስራታቸውንና የብሄራዊም ሆነ ዓለም-አቀፍ የዳታ ጥበቃ ህጋጋት መከተላቸውን ማረጋገጥ፤
- የሳይበር ድንገተኛ ዝግጁነትና ምላሽ ሰጪ ቡድኖች ከብሄራዊና ዓለም-አቀፋዊ ህግጋት ጋር በተጣጣመ መልኩ መረጃን መያዝ የሚችሉባቸውን ስልቶች እና ምርጥ ተሞክሮዎችን በግልጽ ማስቀመጥ፤
- የመረጃ ጥበቃ ህግጋትን ባለመፈጸም ምክንያት የሚመጣ የመረጃ ጥሰት ወይም አግባብነት የሌለው የግል መረጃ አጠቃቀም ቁጥጥር ማድረግ የሚቻልባቸውን ስልቶች መቀየስ፤
- የሳይበር ድንገተኛ ዝግጁነትና ምላሽ ሰጪ ቡድኖች ምርጥ ተሞክሮዎችን እና የጋራ የሆኑ መረጃ መቆጣጠሪያ ፕሮቶኮሎችን በሚስተዋወቁበት ዓለም-አቀፍዊና ክልላዊ ስብሰባዎች ላይ የሚሰሩ ቡድኖችን ማዘጋጀት፤
- ባለድርሻ አካላትን ለማካተት ሲባል መረጃ ጥበቃ ላይ የሚሰሩ ቡድኖች/thematic working groups/ (ለምሳሌ፡- የባንክ ኢንዱስትሪ) መመስረት እና አጠቃላይ የሆነውን የመረጃ ልውውጥን/information exchange/ ማሻሻል፤
- የግል መረጃ በመያዝ ዙሪያ ሊኖሩ የሚችሉ ጥርጣሬዎችን ለማስወገድ በመረጃ ቴክኖሎጂ ልዩ ስልጠና የወሰደ የህግ ባለሙያ መቅጠር ወይም እንዲሳተፍ ማድረግ፤

- ብሄራዊ የተጋላጭነት መረጃ-ቋት ፈጥሮ ቁልፍ ስራዎች ላይ ሊኖር የሚችለውን ተጽእኖ ወይም ወሳኝ የሆኑ ኦፕሬሽኖች የመረበሽ አቅም ወጥነት ባለው ሁኔታ መዳሰስ፤
- ለቁልፍ መረጃ መሰረተ-ልማቶች ቀድሞ ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ ስርዓት የሚገነባ ብሄራዊ ፕሮጀክት ማነሳሳት(መቅረጽ)፤
- ክፍተትን የመድፈን/patch/ እና የተጋላጭነት አስተዳደር (ቅድመ ማስጠንቀቂያ) ስራ የመጀመር መስፈርቶች/deployment requirements ወዘተ) ላይ የሚሰራ ተጋላጭነት ይፋ ማድረጊያ ማዕቀፍ/disclosure framework/ማበልጸግ፤
- ቁልፍ የሆኑ ትግበራዎች የሚመለከታቸው አካላት ክፍተቶቻቸው ከተሸፈነ በኋላ የስርዓቶች ከፍተኛ መናወጥ ለማስወገድ የሚያስችሉ የመሞከሪያ ከባቢዎች ማዘጋጀት፤

### *6.3.6.3. ያሉትን ፖሊሲዎች፣ ሬጉሌሽኖችና አቅሞች ክምችት መመዝገብ*

#### 6.3.6.3.1. የትግበራ መምሪያ

- በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ለዓመታት የለሙትን የፖሊሲዎች ክምችት ማደራጀት (የኤሌክትሮኒክ ኮሙኒኬሽኖች፣ የመረጃ ጥበቃና ደህንነት... ወዘተ)፤
- በተለያዩ ዘርፎች ላይ የሳይበር ደህንነትን ለማሻሻል እስከ አሁን ድረስ የተተገበሩ ሁሉንም ሬጉላቶሪ እርምጃዎችና ያመጡትን ተጽእኖ መለየት፤
- ኦፕሬሽናል የሳይበር ደህንነት ተግዳሮቶችን ለመፍታት የለሙ አቅሞች ክምችት መለየት (ለምሳሌ፡- ብሄራዊ ወይም መንግስታዊ CERTs)፤
- ያሉትን ሬጉሌቶሪ ዘዴዎች መለየት (የመንግስትና የግል ትብብሮች) ከዚያም ግቦቻቸውን በምን ያህል መጠን እንዳሳኩ መዳሰስ፤
- የሳይበር ደህንነት ፖሊሲዎች፣ ሬጉሌሽኖችና ኦፕሬሽኖችን ለማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግስት ተቋማት (ማለትም ሃይልን ሬጉሌት የሚያደርጉ፣ የኤሌክትሮኒክ ኮሙኒኬሽኖችን ሬጉሌት የሚያደርጉ፣ የመረጃ ጥበቃ ባለስልጣናት፣ ብሄራዊ የሳይበር ወንጀል ማዕከላት...ወዘተ) ሚናዎችና ኃላፊነቶች መተንተን፤ ከዚያም መደራረቦችን እና ክፍተቶችን መለየት፤
- አሁን ላይ ያሉ ፖሊሲዎች፣ ሬጉሌቶሪና ኦፕሬሽናል ከባቢዎች የፖሊሲና ስትራቴጂውን ዓላማዎችና አድማስ በምን ያህል መጠን እንዳሟሉ መዳሰስ እና መሻሻል የሚገባቸውን መለየት፤

### 6.3.6.4. ግልጽ የሆነ የአመራር ስርዓት/መዋቅር/ ማልማት

ብሄራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ሊሳካ የሚችለው ግልጽ የሆነ የአመራር ማዕቀፍ ሲኖር ነው፡፡ የአመራር ማዕቀፍ ተገቢ የሆኑ ባለድርሻ አካላትን ሚናዎች፣ ኃላፊነቶችንና ተጠያቂነትን ሊያብራራ የሚችል ነው፡፡ እንዲሁም በፖሊሲና ስትራቴጂው የሕይወት ኡደት ውስጥ ለሚካሄዱ የተለያዩ ተግባራት ለውይይትና ቅንጅት የሚሆን አቅጣጫ ይሰጣል፡፡

#### 6.3.6.4.1. የትግበራ መምሪያ

- ፖሊሲና ስትራጂውን የማስተዳደርና የመገምገም ኃላፊነት የሚወስደው ማን እንደሆነ መወሰን፤
- የፖሊሲና ስትራቴጂው የሳይበር ደህንነት ጉዳዮችን የሚያማክረውን መስተዳድራዊ መዋቅር አማካሪ አካል ማቋቋም፤ በዚህ መዋቅር ውስጥ የሚሳተፉትን መንግስታዊና የግል አካላትን መወሰን፤ሰፊ የሆኑ ባለድርሻዎችን ለመካተት መሞከር፤
- የሳይበር ደህንነት ጉዳዮች አማካሪ አካል ተግባራት በግልጽ ማስቀመጥ፤
- የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ሬጉሌሽን እንዲለሙ የሚያነሳሱ እና/ወይም የሚያለሙ አካላት የተሰጣቸውን የውክልና ተግባራት መግለጽ ወይም ማረጋገጥ፤ እነዚህ አካላት ከአማካሪ አካሉ ጋር እንዴት እንደሚገናኙ እና/ወይም ለአማካሪ አካሉ እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ማብራራት፤
- ስጋቶችንና ተጋላጭነቶችን መቀነስ፣ ለሳይበር ጥቃት መልስ የመስጠት፣ የአደጋ አስተዳደርንና ሌሎችን የማጠናከር ኃላፊነት የወሰዱ አካላት ተግባራት መግለጽ፤እነዚህ አካላት ከአማካሪ አካሉ ጋር እንዴት እንደሚገናኙ እና/ወይም ለአማካሪ አካሉ እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ማብራራት፤ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶችን ጥበቃ ማድረግ፤
- ያሉትን የብሄራዊ የሳይበር ድንገተኛ ክስተቶች ምላሽ ሰጪ ቡድን/CERT/ በደንብ ማጥናት እና መግለጽ፤ እንቅስቃሴዎቻቸውን መቆጣጠር፣ ታማኝነት ባለው መልኩ መረጃ ማጋራት፣ በተከሰቱ ስጋቶች እና ሌሎች ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማት ጥበቃ እንቅስቃሴዎች ላይ መረጃ መስጠት ተግባራትን ማከናወን፤
- የሳይበር ድንገተኛ ክስተቶች ምላሽ ሰጪ ቡድን/CERT/ በብሄራዊና ዓለም-አቀፋዊ ደረጃ ከሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋር የማቀናጀትና ኢንፎርሜሽን በማጋራት ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ማድረግ፤

#### 6.3.6.5. የሳይበር ደህንነት ልምምዶችን ማዘጋጀት

በሳይበር ደህንነት ልምምዶች ብቃት ያላቸው ባለስልጣናት የአደጋ ጊዜ እቅዶች እንዲኖሯቸው፣ ድክመቶች ላይ ኢላማ እንዲያደርጉ፣ በተለያዩ ዘርፎች መካከል ትብብርን መፍጠር እንዲችሉ፣ ቀጣይነት ባለው እቅድ ላይ መሻሻልን ለማምጣት እና ከድንገተኛ ክስተት ቶሎ ማገገምን ለማሳደግ ሲባል የትብብር ባህልን ለማመንጨት ያስችላቸዋል፡፡ የሳይበር ደህንነት ልምምዶች ማህበረሰቡ ለተፈጥሮ አደጋዎች፣ ለቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶች ውድመት፣ ለሳይበር ጥቃቶችና ለአስቸኳይ ጊዜ ምን ያህል ዝግጁ እንደሆነ ለማወቅ ጠቃሚ መሳሪያዎች ናቸው፡፡

##### 6.3.6.5.1. የትግበራ መምሪያ

- ተከታታይ የሆኑ የሳይበር ልምምዶች ተጽእኖ መዳሰስ ከዚያም የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂውን ፍላጎት ይበልጥ ለማሳካት በሚያስችል ሁኔታ ራዕይን ማሻሻል፤
- ሊሳኩ የሚችሉ ተጨባጭ ዓላማዎች ያሉት የሳይበር ደህንነት ልምምዶች የመካከለኛ ወቅት ተልዕኮ ማልማት፤
- በሂደቱ ውስጥ መካተት ያለባቸውን ተገቢ የመንግስትና የግል ዘርፍ ባለድርሻ አካላት መለየት፤
- ለእያንዳንዱ የሳይበር ደህንነት ልምምድ የሚከተሉት መደረግ አለባቸው፡-
  - የልምምዱን አስተዳዳሪ(ዎች) ለይቶ መግለጽ፤
  - ልምምዱን የሚያዘጋጅና ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚወስን እቅድ አውጪ ቡድን ማዋቀር፤
  - ሊደረስባቸው የሚፈለጉ ተጨባጭ ዓላማዎችን መግለጽ፤ሁልጊዜ ከሚሞከሩት የድንገተኛ እቅዶች ጋር ማዛመድ፤
  - በልምምዱ አጭር የድርጊት ገለጻ ላይ መስማማት፤ አጭር የድርጊት ገለጻው ሊተገበር የሚችል እና በእውነተኛ ክስተቶች ላይ የተመሰረተ መሆኑን ማረጋገጥ፤
  - መከተል የሚገባን የግምገማ እና የፍተሻ አካሄድ ላይ መስማማት፤
  - ግልጽ የሆነ የሚዲያና የህዝብ ግንኙነት ጉዳዮች ስትራቴጂን ለይቶ መግለጽ፤
  - ከዓለም-አቀፍ ትብብሮችና የታዛቢዎች ፕሮግራም ጋር መስማማት፤
  - የልምምዱን ተዋንያኖች መለየትና ማሳተፍ፤
  - ተዋናዮቹን ከልምምዱ ገጽታዎች ጋር የሚያላምድ የስልጠና ፕሮግራም መንደፍ፤

- ልምምዱ በተገቢ ሁኔታ መዘጋጀቱን ለማረጋገጥ የሙከራ ሂደት ማዘጋጀትና ማስፈጸም፤
- ልምምዱን ማስኬድ፤ እድገቱን መገምገምና መቆጣጠር፤
- ልምምዱ ካበቃ በኋላ ማጠቃለያ ፕሮግራም በማዘጋጀት ዋና ዋናዎቹን መደምደሚያዎችና የተገኙ ትምህርቶችን መሰብሰብና አንድ ላይ ማጠናቀር፤
- ስለስኬቶች፣ ቁልፍ ግኝቶች እና ስለተገኙ ትምህርቶች ሪፖርት በማድረግ በአጭር ወይም ማጠቃለያ ሪፖርት ሊታተም የሚችል ዝርዝር የሆነ ሪፖርት ማዘጋጀት፤ (በልምምዱ ተዋናዮች መካከል ምስጢራዊ ሆኖ ሊቆይ ይገባል)፤
- የተገኙትን ትምህርቶች እና ቁልፍ ምክረ-ሀሳቦች መከታተል ከዚያም ኢላማ የተደረጉት ባለድርሻ አካላት እንደሚተገብሯቸውን ማረጋገጥ፤

#### 6.3.6.6. መነሻ የሚሆን የደህንነት መስፈርቶችን መፍጠር

ሁሉም ወሳኝ መንግስታዊና ግላዊ ድርጅቶች የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶቻቸው የአደጋ ዳሰሳ ተደርጎ ካለቀ በኋላ የተገኙ ስጋቶች፣ተጋላጭነቶች እና አደጋዎች ለመቀነስና ለመከላከል አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡ መነሻ የሚሆኑ የሳይበር ደህንነት መስፈርቶች ሁሉም ተቋማት የሚተገብሯቸው ዝቀተኛ የደህንነት ደረጃዎች ናቸው፡፡

##### 6.3.6.6.1. የትግበራ መምሪያ

- እስከ ዛሬ ሲወሰዱ የነበሩትን የሳይበር ደህንነት መለኪያዎች በሙሉ መከለስና ማሻሻል፡-
  - አሁን ላይ ባሉት የቁጥጥር ሰነዶች ውስጥ የተገለጹ የደህንነት መለኪያዎችን መለየት፤
  - የመረጃ ደህንነት ስጋቶችን በመለየት ስጋቶች ካሉት ከመለኪያዎች ጋር ማቆራኘት፤
  - ካሉት ቴክኒካል ስታንዳርዶች (ለምሳሌ፡- ISO27001, ISO27002, ISO27004, COBIT, ITIL,ወዘተ) በመጠቀም ክፍተቶችን መለየትና የክፍተቶቹን መቀነሻ እርምጃዎችን ማምጣት፤ ክፍተቶች ከተገኙ የባለሙያዎች አስተያየትና ተገቢ ስታንዳርዶችን ግምት ውስጥ በማስገባት የመለኪያ ዝርዝሮቹን ማሻሻል፤
- የደህንነቱን እድገት የሚያሳዩ በራሳቸው ዳሰሳ ማድረግ የሚችሉ መሳሪያዎችን መፍጠርና ባለድርሻ አካላት እንዲጠቀሟቸው ማበረታታት፤

- ዝቅተኛ የመለኪያዎች ዝርዝር መሰረት በማድረግ የመረጃ ደህንነት ምርመራዎችን ለሌሎች መስጠት፤.
- ትልቅ ተጽእኖ ስላላቸው ክስተቶች የቀረበውን ሪፖርት በመንተራስ መነሻ መስፈርቶችን ማሻሻል፤

## 6.4. የሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት

### 6.4.1. መግቢያ

የሳይበር መሰረተ ልማቶችንና ቴክኖሎጂዎችን በማበልጸግ፣ የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ ሽግግሮች እና አዳዲስ ፈጠራዎች በማስፋፋት፤ እንዲሁም በተለያዩ ደረጃዎች ሃገር በቀል እና አለም አቀፍ ምርምር እና ልማት ተግባራት ማከናወን ተገቢ ነው። በመሆኑም በዘርፉ የራስ አቅም እንዲኖር፣ የሳይበር ቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ስራዎች በተደራጀ ጥናት እና ምርምር በመደገፍ የሳይበር ደህንነት ኢንዱስትሪ ለመገንባት ይሰራል። ይህንን የትኩረት አቅጣጫ ለማሳካት የሚከተሉት ግቦች እና የትግበራ መምሪያ በመለየት በልዩ ትኩረት መንግስት ይንቀሳቀሳል።

### 6.4.2. ግቦች

1. ቁልፍ የመረጃ መሰረተ ልማቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ምርቶችና አገልግሎቶች በምርምርና ልማት ላይ የተመሰረቱ ማድረግ፤
2. የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶች፣ ስጋቶች እና ጥቃቶች መንስዔዎቻቸውን በጥናትና ምርምር መለየት፤ መፍትሄዎች ማቅረብ፤
3. የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ ሃገር በቀል ዕውቀት እና ፈጠራዎችን መሰረት ያደረገ የምርምር እና ልማት አቅም መገንባት፤
4. በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ እና የተቀናጀ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት ባህል መገንባት፤

### 6.4.3. አድማስ

የዚህ የትኩረት አቅጣጫ አድማስ የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ ሃገሪቱ ማከናወን የሚገባት የምርምርና ልማት ተግባራትን የሚያጠቃልል ነው።

### 6.4.4. መስፈርት

የሳይበር ደህንነት አጀንዳ ማንሳት፣ በተነሳው አጀንዳ ላይ ምርምር ማድረግ ከዚያም የተገኘውን ውጤት እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ወደ ተግባር እንዲለውጥ መስራት ነው።

### 6.4.5. ቁጥጥር

ይህ የትኩረት አቅጣጫ ተሳካ የሚባለው የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ የሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት ጉዳዮችን ማንሳት ሲችሉ፤ምርምሮች በመንግስታዊና በግል ዘርፎች ቅንጅት ሲሰሩ፤ በምርምር የተገኙ ውጤቶች ወደ ተግባር ተለውጠው በዘርፉ ጠንካራ የሆነ የሳይበር ደህንነት አቅም ሲገነባ ነው።

### 6.4.6. የትግበራ መምሪያ

- የመካከለኛ ጊዜ አድማስ ያላቸው የሳይበር ደህንነት ዓላማዎችን ያማከሉ የምርምርና ልማት አጀንዳ መፍጠር፤
- በሳይበር ኢንዱስትሪዎች ለተሰማሩ አካላት መድረክ መፍጠር እና በምርምርና ልማት እንዲታዩ ስለሚፈልጓቸው ርዕሶች ጥያቄ ማቅረብ፤
- ከፍተኛ ደረጃ ያለው የምርምር ስራ ውስጥ የግሉ ዘርፍ ተሳታፊ እንዲሆን በማበረታታት የመንግስትና የግል ተቋማት የምርምርና ልማት አጋርነት መፍጠር፤
- ከዓለም-አቀፍ የሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት ተቋማት ጋር አጋርነት ወይም ትብብር ማድረግ፤
- የተለያዩ ተቋማት በሚያከናውኗቸው የምርምር መርሀ-ግብሮች መካከል መደራረቦችን ለማስቀረት የምርምር ቅንጅት እቅድ ማዘጋጀት፤
- የሳይበር ደህንነት ምርምር በሁሉም ቦታ እንዲገኝ ውጤታማ የሆኑ ማበረታቻዎችን በማዘጋጀት ግለሰቦችና ድርጅቶች የእነዚህ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤

## 6.5.የዲጂታል ማንነትና ግላዊ መረጃ ጥበቃ

### 6.5.1. መግቢያ

ዲጂታል ማንነት እና ግላዊ መረጃዎች ተገቢ የሆነ ትኩረት እና ጥበቃ ካልተደረገላቸው በዜጎች ላይ የሚደርስ የሳይበር ጥቃት እንዲስፋፋ፤ ማንነት ተኮር ጥቃቶች እንዲበራከቱ፤ እንዲሁም ከማህበረሰቡ ባህልና እሴት ያፈነገጡ ክስተቶች የዜጎች የግል ሕይወትና ሰብዓዊ መብቶች ስጋት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል። ስለሆነም መንግስት በዜጎች ላይ ያነጣጠሩ የስነ-ልቦና ጥቃቶች ለመከላከል፤ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ፤የዲጂታል ማንነትና የግላዊ መረጃ ስጋትናተጋላጭነት ለመቀነስ፤እንዲሁም ዜጎች ለግል መረጃ ልውውጥ

የሚጠቀሟቸውን የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶች ደህንነት ለመጠበቅ ይህንን የትኩረት አቅጣጫ ይተገብራል፡፡

### 6.5.2. ግቦች

1. በዜጎች ዘንድ ታዓማኒነት ያለው የዲጂታል አገልግሎት እና ግላዊ መረጃ ጥበቃ እንዲኖር ማድረግ፤
2. በታዳጊዎች ላይ የሚደርሱ የሳይበር ስጋቶችን፣ ተጋላጭነቶችንና ጥቃቶችን መከላከል፤ በኢትዮጵያ ማህበረሰብ እሴቶችና በመልካም ስብዕና ታንፀው እንዲያድጉ ሳይበር ሊጫወት የሚገባውን ገንቢ ሚና ማሳደግ፤
3. በሳይበር ምህዳር ላይ የሚደርስ ጾታዊ ጥቃት፣ ወሲባዊ ትንኮሳ፣ የሥነ-ልቦና ተፅዕኖ መከላከል እና መቀነስ፤
4. ማንነትን መሰረት ያደረጉ በዲጂታል የሚፈጸሙ የሃይማኖት ጽንፈኝነት፣ የብሄር ተኮር ጥቃቶችንና የመሳሰሉትን መግታትና መከላከል፤

### 6.5.3. አድማስ

ይህ የትኩረት አቅጣጫ የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ በሃገሪቱ መከናወን ስለሚገባቸው የዲጂታል ማንነት እና ግላዊ መረጃዎች ተግባራት ዙሪያ የሚያተኩር ነው፡፡

### 6.5.4. መስፈርት

የዜጎችን የስነ-ልቦና ጥቃቶች መከላከል፤ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፤የዲጂታል ማንነትና የግላዊ መረጃ ስጋትና ተጋላጭነት መቀነስ፤እንዲሁም ዜጎች ለግል መረጃ ልውውጥ የሚጠቀሟቸውን የመረጃ መሰረተ-ልማቶች ደህንነት መጠበቅ ነው፡፡

### 6.5.5. ቁጥጥር

ይህ የትኩረት አቅጣጫ ዓላማውን አሳካ የሚባለው በዜጎች ላይ የሚደርሱ ማንነትን መሰረት ያደረጉ የሳይበር ጥቃቶች መከላከልና ግላዊ መረጃ ጥበቃ ዙሪያ የሚያጋጥሙ የሳይበር ደህንነት ስጋትና ተጋላጭነት መቀነስ ሲቻል ነው፡፡

### 6.5.6. የትግበራ መምሪያ

የግላዊ መረጃ ደህንነት ማረጋገጥ የሚያስችሉ አቅሞች፣ ተቋማዊ ማዕቀፎች ማልማት፣ የህግ እና የቁጥጥር አሰራር ስርዓቶች በቅንጅት ተግባራዊ ማድረግ፤

## 6.6. ቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማት ጥበቃ

### 6.6.1. መግቢያ

መረጃ ውድ ሃብት እየሆነ በመምጣቱ ቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማቶችን እና ተቋማትን ከሳይበር ጥቃቶች መከላከል፤ የሳይበር ስጋቶችንና ተጋላጭነቶችን መቀነስ፤ የሳይበር ጉዳት ሲደርስ በፍጥነት መልሶ ማቋቋም አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በአግባቡ ለመምራትና ለመተግበር፣ ከውድመት ለመከላከል፤ እንዲሁም የሳይበር ምህዳሩን ደህንነት ለማረጋገጥ እና ተዓማኒነቱን ለማሳደግ ቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማቶች ጥበቃ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ለዘርፉ ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው፡፡ይህንን የትኩረት አቅጣጫ ለማሳካት የሚከተሉት ግቦች እና የትግበራ መምሪያ በመለየት መተግበር አስፈላጊ ነው፡፡

### 6.6.2. ግቦች

1. ቁልፍ መሰረተ-ልማቶች እና ተቋማት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶች፣ ጥቃቶችና ውድመቶችን የመለየት፣ የመከላከል እና ምላሽ የመስጠት አቅም ማጎልበት፤
2. ከውጭ የሚገቡ እና በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማት ምርቶችና አገልግሎቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፤
3. ለቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማቶች ልዩ ጥበቃ ለማድረግ የመንግስት እና የግል ዘርፍ ትብብር እና ቅንጅት መፍጠር፤

### 6.6.3. አድማስ

ይህ የትኩረት አቅጣጫ በሃገሪቱ ውስጥ ያሉትን ቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማቶችን መለየትና ለሳይበር ስጋቶችና ጥቃቶች ተጋላጭ እንዳይሆኑና አደጋ እንዳይደርስባቸው ተገቢውን መከላከልና ጥበቃ ማድረግ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

### 6.6.4. መስፈርት

ቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማቶችን በመለየት ተገቢ የሆኑ የሳይበር ደህንነት ዘዴዎችን በመጠቀም ስጋቶቻቸውን መቀነስ እና አደጋዎቻቸውን መከላከል ነው፡፡

### 6.6.5. ቁጥጥር

ይህ የትኩረት አቅጣጫ ዓላማውን አሳካ የሚባለው በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማቶች ተለይተው አስፈላጊ የሆነ የሳይበር ደህንነት ጥበቃ ሲደረግላቸው ነው፡፡

### 6.6.6. የትግበራ መምሪያ

1. ቁልፍ የሆኑ መሰረተ ልማት ተቋማትን መለየት፣ የማይበገር የመከላከል ዓቅም መፍጠር፣ የቁልፍ መሰረተ ልማቶች ህጋዊ፣ ተቋማዊና ቴክኒካዊ ቀጣይነት ያላቸው እርምጃዎች ለመውሰድ የሚያስችሉ ማዕቀፎች እና አገልግሎቶች መፍጠርና ማበልጸግ፤
2. ቁልፍ የመሰረተ ልማት ተቋማት ሚናና ሃላፊነቶች የሚመለከታቸው የመንግስት እና የግል ተቋማት፣ እንዲሁም የግለሰብ እና የጋራ ሃላፊነቶች እና ግዴታዎች ሁሉን አቀፍ በሆነ ሁኔታ በህግ ወይም በስታንደርድ መልክ መስፈርቶች በማዘጋጀት እንዲተገበር ማድረግ፤
3. ቁልፍ የመሰረተ ልማቶች ጥበቃ ለማድረግ የሚያስችሉ የመረጃ ልውውጥ ስርዓቶች እና ማዕቀፎች ማዘጋጀት/ማበልጸግ፤

#### *6.6.6.1. ብሄራዊ የሳይበር ደህንነት አማራጭ እቅዶችን ማልማት*

ብሄራዊ የሳይበር ደህንነት አማራጭ እቅዶች የሚባሉት ቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማቶችን የሚያካትቱ ዋና ክስተቶች ሲከሰቱ መልስ ለመስጠት፤ እንዲሁም ክስተቶቹን ተከታትሎ አገልግሎቶች እንዲያገግሙ ማድረጊያ ጊዜያዊ መዋቅሮችና እርምጃዎች ናቸው። ብሄራዊ የሳይበር ደህንነት አማራጭ እቅድ የጠቅላላው ብሄራዊ አማራጭ እቅድ አካል መሆን አለበት። በተጨማሪም የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ወሳኝ አካልም ነው።

##### 6.6.6.1.1. የትግበራ መምሪያ

- ስጋቶችንና ተጋላጭነቶችን መለየትንና ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተጽእኖ እንዲሁም ቀደምትነቶችን የሚሸፍን መነሻ የስጋት ዳሰሳ ማድረግ፤
- ተገቢ ባለድርሻ አካላትን በሂደቱ ውስጥ ማሳተፍ፤ ይህም ሚናዎቻቸውና ኃላፊነቶቻቸው ግልጽና ያልተደራረቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- የተለያዩ አስጊ ሁኔታዎች በሚገጥሙበት ጊዜ ሁሉም ተገቢ ባለድርሻ አካላት የሚጠቀሟቸውን የስታንዳርድ ኦፐሬትንግ አካሄዶች /standard operating procedures/ ማልማት፤
- አስፈላጊ የትብብርና መልስ የመስጫ ማዕቀፍ ማልማት፤ (ለምሳሌ፡- አቅም ግንባታዎች፣የስታንዳርድ ኦፐሬትንግ አካሄዶች/standard operating procedures/፣ መረጃን ያለፈቃድ ይፋ ያለማድረግ ስምምነት ወዘተ…)

- በአስቸኳይ ሁኔታዎች ጊዜ ሚዲያን ለመቆጣጠር የምንጠቀማቸውን የስታንዳርድ ኦፐሬቲንግ አካሄዶች መግለጽ፤
- የስታንዳርድ ኦፐሬቲንግ አካሄዶች፣ አቅሞችንና ዘዴዎችን መሞከር፣ መገምገም እና ማስተካከል፤
- አቅሞችን ለመስጠት ኃላፊነቱን የሚወስድ ሰራተኛ ማሰልጠን፤
- አሁን ያሉትን ስታንዳርድ የመስሪያ ቅደም-ተከተሎችን፣ ሚናዎችን፣ ኃላፊነቶችን እና የኮሙኒኬሽን ዘዴዎች የሚገመግሙ ልምምዶችን መዘጋጀትና መፈጸም፤.
- ከሳይበር ደህንነት ልምምዶች የተወሰዱ ትምህርቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት አማራጭ እቅዱን መከለስ፤

### 6.6.6.2. ብሄራዊ የስጋት ዳሰሳ አካሄድን መከተል

- ከተቻለ መጠቀም በሚገባን የስጋት ዳሰሳ ዘዴ ላይ መስማማት ካልተቻለ ደግሞ ያሉትን ለብሄራዊ ስጋቶች በሚስማማ መልኩ ማዘጋጀት፤
- ስጋትን ለመለየትና ለመዳሰስ "ሁሉም አደጋ ነው/all-hazard/" የሚለውን አካሄድ መከተል፤
- ቁልፍ ዘርፎችን መለየትና ለዘርፎቹ የሚስማማ የመከላከያ እቅድ ማዘጋጀት። ይህም የሚከተሉትን ተግባራት ሊይዝ ይችላል፡-
    - ህብረተሰቡና ኢኮኖሚው በሚገባ መስራት የሚያስችሉትን ቁልፍ ሀብቶችን/assets/ እና አገልግሎቶችን መለየት፤
    - ቁልፍ ሀብቶች ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩትን ሁሉንም ስጋቶችን መዳሰስ፤ በሚፈጥሩት ተጽእኖ መሰረት በቅደም-ተከተል ማስቀመጥ እና እውን የመሆን እድላቸውን ማስላት፤
    - ትክክለኛ የሆኑትን የግሉ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ የተደረጉ የስጋት ዳሰሳዎች ማጋራት እና ከግኝቶች ጋር ዝምድና መፍጠር፤
    - የትኞቹን ስጋቶች እንዳሉ መውሰድ እንደሚቻል፣ የትኞቹን ስጋቶች እንዴት መቀነስ እንደሚገባ፣ እንዲሁም ምንም ሊደረጉ የማይችሉ ስጋቶችን በተመለከተ ውሳኔ መወሰንና ለምን እነዚህ ውሳኔዎች እንደተወሰዱ ግልጽ ማድረግ፤
    - የተለዩትን ስጋቶች የሚይዝ ብሄራዊ የስጋት መዝገብ ማዘጋጀት፤
    - ቀጣይነት ባለው መልኩ ስጋቶችንና ተጋላጭነቶችን ለመቆጣጠር እና ብሄራዊ የስጋቱን ስፋት ለማሻሻል ተደጋጋሚ የሆነን ሂደት መግለጽ፤

## 6.7. ሃገር-አቀፍ እና ዓለም-አቀፍ ትብብር

### 6.7.1. መግቢያ

የሳይበር ደህንነት ጥቃት እጅግ ውስብስብ፣ ኢ-ተገማች፣ ተለዋዋጭና ድንበር የለሽ ከመሆኑ የተነሳ በመንግስትና በተወሰኑ ተቋማት ብቻ መፍትሄ የሚያገኝ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ ሃገራዊ ቅንጅት እና አጋርነት መመስረት፤ በሳይበር ደህንነት ላይ የተጋረጡ ስጋቶችን መከላከል የሁሉም የመንግስትና የግል ዘርፍ (ባለድርሻ አካላት) የጋራ ኃላፊነት ነው፡፡ እንዲሁም የሳይበር ደህንነት ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው በመሆኑ፤ ከምህዳሩ ተለዋዋጭነትና ድንበር የለሽነት ባህሪ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶችና ጥቃቶች ለመከላከል ዓለም አቀፍ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስታንደርዶች፣ ልምዶች እና አመለካከቶች የተለያዩ በመሆናቸው የሳይበር ደህንነትን ከማረጋገጥ አንጻር ከፍተኛ ተጽዕኖ እያደረገ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ይህንን የትኩረት አቅጣጫ ለማሳካት የሚከተሉት ግቦች እና የትግበራ መምሪያ በመለየት መተግበር አስፈላጊ ነው፡፡

### 6.7.2. ግቦች

1. ሃገራዊ ሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ በመንግስት፣ በግሉ ዘርፍ እና በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅትና አጋርነት መመስረትና ማጠናከር፤
2. የሳይበር ደህንነት ምርት በማምረትና አገልግሎት በማቅረብ ላይ የተሰማሩ ሃገር በቀል የግል ተቋማት እንዲበራከቱና እንዲጠናከሩ በማድረግ የሃገሪቱን የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎት ፍላጎት ከማርካት አልፈው በዓለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል፤
3. የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ ስለላ እና መሰል ዓለም-አቀፍ ይዘት ያላቸው የሳይበር ደህንነት ስጋቶች ለመከላከል ትብብር መፍጠር፤
4. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የሚደረግ ዓለም አቀፍ ትብብር የሃገሪቱ የውጪ ጉዳይ ዲፕሎማሲ አካል እንዲሆን ማድረግ፤
5. ሁለትዮሽና ከዚያ በላይ የሆኑ የሳይበር ደህንነት ስምምነቶችን ማበረታት እና ማጎልበት፤

### 6.7.3. አድማስ

ይህ ትኩረት አቅጣጫ የሳይበር ደህንነት አጀንዳዎችን በተመለከተ በሃገር-አቀፍ እና በዓለም-አቀፍ ደረጃ ትብብርና ቅንጅት በመፍጠር ዙሪያ የሚያተኩር ነው፡፡

### 6.7.4. መስፈርት

በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ሰፊ ልምድ እና ጥሩ ተሞክሮ ያላቸውን አካላት፣ ድርጅቶችና ሃገሮች በመለየት ጠንካራ የሆነ ትስስር በመፍጠር የሳይበር ስጋቶችንና ጥቃቶችን የመቀነስና የመከላከል አቅም ማጎልበት ነው፡፡

### 6.7.5. ቁጥጥር

ይህንን የትኩረት አቅጣጫ ለማሳካት በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ሰፊ ልምድና ጥሩ ተሞክሮ ያላቸው ሃገራዊ እና ዓለም-አቀፍ አካላት በመለየት ጠንካራ ትስስር ተመስርቶ ከትስስሩ ተጠቃሚ መሆን ሲቻል ነው፡፡

### 6.7.6. የትግበራ መምሪያ

- ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ መኖሩ ኢትዮጵያ ዓለም-አቀፍ ትብብርን በተመለከተ ያላትን አቋም የሚጠቁም በመሆኑ ዓለም-አቀፍ ትብብርን ለማጎልበት የሚያስችሉ ስልቶችን መቀየስና መተግበር፤
- የሳይበር ደህንነት ትብብር ለማድረግ የሚፈልጉ ሃገራትን በመለየት፣ ለምን ትብብር መፍጠር እንዳስፈለገ አቅጣጫ ማስቀመጥ፤(ለምሳሌ፡- የሳይበር ወንጀል፣ ኦፐሬሽናል እና ሌሎችም)፤
- ዓለም-አቀፍ ትብብር የሚያደርጉ የሚመለከታቸውን ድርጅቶች(መ/ቤቶች) በብሔራዊ ደረጃ መለየት፣ተግባራትን በዝርዝር መስጠት፣ ተግባራዊ እንዲሆን ክትትል ማድረግ፤
- መረጃ መጋራት(ለምሳሌ፡- ቤንችማርክ በማድረግ፣ ቴክኖሎጂያዊ እውቀት እና በመሰረታዊ የስጋት ዳሰሳዎች)፣ ብዙ አገራትን ባሳተፈ ከፍተኛ ደረጃ ያለው የመንግስት፣ የግል አጋርነት እና መረጃ የማጋራትና የመተንተን አቅም ባላቸው ማዕከላት አማካኝነት ዓለም-አቀፍ ትብብር መፍጠር፤
- ከመረጃ ደህንነት ጋር የተያያዘ ሆኖ ከብሄራዊ ደህንነት ጥቅሞች ተቃራኒ እስካልሆነ ድረስ ሁለትዮሽ፣ ብዙዮሽ ወይም ዓለም-አቀፍ ስምምነቶችን እና ኮንቬንሽኖችን መቀላቀል፤
- ተጨባጭና ዋና አገር አቋራጭ የሆኑ ስጋቶችን በተመለከተ መረጃ ለመጋራትና መልስ ለመስጠት የሚያግዙ የስታንዳርድ ኦፐሬቲንግ አካሄዶች (standard operating procedures(SOPs) ለመቅረጽ በሚደረጉ ዓለም-አቀፍ ጥረቶች ላይ አስተዋጽኦ ማድረግ፤

- ከሳይበር ደህንነት ስትራቴጂያዊ አጋሮች ጋር የሚደረግን ትብብር መነሻ እንዲሆን አካባቢያዊ፣ አህጉራዊና ዓለም-አቀፋዊ ተሳትፎን ማበረታታት፤

### 6.7.6.1. በመንግስትና በግሉ ዘርፍ አጋርነት መፍጠር

የመንግስት እና የግሉ ዘርፍ የተጋሯቸውን ግቦች ለማሳካት የጋራ የሆነ ዓላማዎችን በመንደፍ፤የደህንነትና ከስጋት ቶሎ ለማገገም የሚያስችሉ የተለያዩ ገጽታዎች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ተግባራት እንደሚከተሉት ናቸው-

- ወንጀል እንዳይሰራ ማድረግ(ጥቃት ፈጻሚዎችን ጥቃት ከመፈጸም ማገድ)፤
- መከላከል (አዲስ ስጋት ሲኖር ጥናትና ምርምር ማድረግ)፤
- መለየት (ለአዳዲስ ስጋቶች መፍትሄ ለማግኘት ኢንፎርሜሽን መጋራትን ማከናወን)፤
- መልስ መስጠት (አንድ ክስተት መጀመሪያ ላይ ያመጣውን ተጽእኖ ለመቋቋም የሚያስችል አቅም መፍጠር)፤
- ማገገም (አንድ ክስተት መጨረሻ ላይ የፈጠረውን ተጽእኖ ለመጠገን የሚያስችል አቅም መፍጠር)፤

#### 6.7.6.1.1. የትግበራ መምሪያ

- መረጃ ለመጋራትና የሙያ ልቀትን ለማግኘት እና ድግግሞሽን ለማስቀረት በመንግስትና በግሉ ዘርፍ መካከል ያለውን አጋርነት ከሌሎች ድርጅቶች ጋር እንዴት ትስስር መፍጠር እንደሚቻል እቅድ ማውጣት፤
- ትብብር ለማድረግ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን እና ማዕቀፎች ማዘጋጀት/ማጽደቅ፤.
- የሚመለከታቸው አካላትን ለመረዳትና ንቃተ-ህሊና ለማጎልበት ሲባል በከፍተኛ ባለስልጣኖች ደረጃ ስትራቴጂያዊ ትብብር የመፍጠርን ጥቅም ማሰስ፤
- በድርጅታቸው ኃላፊነት ተስጥቷቸው በተለያዩ የሳይበር ደህንነት ዙሪያ እርምጃ መውሰድና መቀየር የሚችሉና ታማኝ የሆኑ ልዩ ባለሙያዎችን መመልመል፤
- የመንግስት-የግል ትብብር ለማድረግ የሚያስችሉ የህግ እና ቴክኒካል ማዕቀፎች በማዘጋጀት/በማበልጸግ/በህግ የመወሰን ስልጣን እንዲኖር ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የህግ ምክር መስጠት፤
- ከህግ አማካሪ ጋር በመሆን የአባልነት ደንቦችና መስፈርቶች የሚያብራራ መረጃን ይፋ ያለማውጣት ስምምነት/non-disclosure agreement/ ናሙና ማዘጋጀት፤ ይህንን ስምምነት በመጠቀም የሚመለከታቸው አካላትም እንዲፈርሙት መጠየቅ፤

- ሁሉም የትብብሩ አባላት ንቁ ተሳታፊ በመሆን ለአባልነቱ ተገቢ እሴት ያላቸውን ኢንፎርሜሽንና፣ አገልግሎቶች መስጠታቸውን እና ድጋፍ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ፤
- ድንበር ተሻጋሪ የሆነ መረጃ የመጋራትና ቅንጅት በመፍጠር ከሌሎች የመንግስት-የግል ትብብሮች ጋር ዓለም-አቀፍ ግንኙነቶችን ለመፍጠር እድሎችን መፈለግ፤

### *6.7.6.2. ባለድርሻ አካላትን መለየትና ማሳተፍ*

ስኬታማ በሁነ ሁኔታ ብሄራዊ ሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ለመተግበር በመንግስትና በግል ባለድርሻ አካላት መካከል ተገቢ የሆነ ትብብርን ይሻል፡፡ ለፖሊሲና ስትራቴጂው ስኬት ባለድርሻ አካላትን መለየትና ማሳተፍ ወሳኝ የሆነ እርምጃ ነው፡፡ የመንግስት ባለድርሻ አካላት በአብዛኛው የፖሊሲ፣ የሬጉሌቶሪና የኦፐሬሽናል የውክልና ስልጣን አላቸው፡፡ የሃገሪቱን መሰረተ-ልማቶች እና አገልግሎቶች ጤንነት እና ደህንነት ያረጋግጣሉ፡፡ የግሉም ዘርፍ የልማት አካል መሆን ስላለባቸው አብዛኛዎቹ ቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማቶችና አገልግሎቶች እነርሱን ባካተተ ሁኔታ የወደፊት ዕቅድ አካል አድርጎ መለየት ተገቢ ነው፡፡

#### 6.7.6.2.1. *የትግበራ መምሪያ*

- ሁሉንም የቁልፍ መሰረተ-ልማቶችና አገልግሎት ሰጪ አካላትን በአግባቡ መለየት፤
- የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ስርዓቶችን ለማነሳሳት እና ለማልማት ኃላፊነት ያለባቸውን የመንግስት ባለድርሻ አካላት መለየት፤ ለምሳሌ፡- ብሄራዊ ቴሌኮሙኒኬሽኖችን ሬጉሌት የሚያደርግ፣ ብሄራዊ መሰረተ-ልማቶችን መጠበቂያ ማዕክል፣ ወዘተ)፤
- በግልጽ ሚናዎቻቸውንና ኃላፊነቶቻቸውን በማስቀመጥ የመንግስትና የግል ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ (ለምሳሌ፡- የግል ባለድርሻ አካላት መሰረተ-ልማቶቻቸውን ጥበቃ ያደርጋሉ፤ ሆኖም ብሄራዊ ደህንነት ጥበቃ ዙሪያ የጋራ የሆነ ኃላፊነት ይኖራቸዋል)፤
- የመንግስትና የግል ባለድርሻ አካላትን በሂደቱ ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን የሚያስችል ተገቢ የሆነ ማበረታቻ ማስቀመጥ (ለምሳሌ፡- የግሉን ዘርፍ ተሳታፊ የሚያደርጉ የሚያስወጡ ሬጉሌሽኖች ማውጣት)፤ እንዲሁም የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ሊኖሯቸው የሚችሉትን ልዩነትና የፍላጎት መጋጨት ግምት ውስጥ ማስገባት፤
- ፖሊሲና ስትራቴጂው ትግበራ ትክክለኛ ባለድርሻ አካላትን በትክክለኛ ጊዜ በሂደቱ ውስጥ ማሳተፍ፤

- ባለድርሻ አካላት ለፖሊሲና ስትራቴጂው ዓላማዎች ለምንና እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ፣ የግለሰቦችን ተግባራትና የድርጊት መርሀ-ግብሮችን መግለጽ (ስጋቶችንና አደጋዎችን ለመዳሰስ ከቁልፍ መሰረተ-ልማት ባለቤቶችና ቁልፍ አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር የቅንጅት አካሄድ መከተል)፤
- በብሄራዊ ደረጃ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሳይበር ደህንነት ጉዳዮችን ማሳለጥ የሚያስችል ሚና መስጠት፤ (ለምሳሌ መረጃ መጋራት፣ ዓለም-አቀፍ ትብብር፣ ስጋትን ማስተዳድር)፤
- የባለቤትነት ስሜት ለመፍጠርና ለእያንዳንዱ ተወካይ አማራጭ ለመመደብ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን ተወካዮች ማሳተፍ፤
- በብሄራዊ ደረጃ ንቃተ-ህሊናን ከፍ በማድረግ ዜጎች የሳይበር ደህንነት ስጋቶች በደንብ እንዲረዱ፤ እንዲሁም ስጋቶቹ ከመከሰታቸው በፊት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ማድረግ፤
- እንደ ሃገር መከላከያ፣ የውጪ ጉዳዮች፣ፍትህ፣ ቴሌኮሙኒኬሽን ተቆጣጣሪ፣ የመረጃ ጥበቃ ባለስልጣን፣ እና የሳይበር ወንጀል መምሪያ ያሉትን ተቋማት የሳይበር ደህንነት ቀውሶችን ማስተዳደር፣ ከጉዳት ነጻ መሆን ያለባቸውን ሚኒስትር መስሪያ ቤቶች በፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራ ላይ ተሳታፊ ማድረግ፤
- በብሄራዊ ደረጃ የመረጃ መጋራት አቅሞች ቁልፍ አካል ሊሆኑ ስለሚችሉ አሁን ላይ ያሉትን ብሄራዊ የሳይበር ዝግጁነትና ምላሽ ሰጪ ቡድኖች (CERTs) ማሳተፍ፤
- የተለያዩ የባለድርሻ አካላት ቡድኖችን ፍላጎት ለማካተት ብሄራዊ ፍላጎት ያላቸውን ቡድኖች ማሳተፍ፤

### *6.7.6.3. የሚታመኑ የመረጃ መጋሪያ ስርዓቶች መዘርጋት*

ያለማቋረጥ ተለዋዋጭ የሆነ ከባቢን ይበልጥ ለመረዳት በግልና በመንግስት ባለድርሻ አካላት መካከል የመረጃ መጋራት ጠቃሚ ዘዴ ነው። መረጃ መጋራት ቁልፍ በሆኑ የመንግስትና የግል ባለድርሻ አካላት መካከል ስትራቴጂያዊ ትብብር መፍጠሪያ መንገድ ነው። የቁልፍ መሰረተ-ልማት ባለቤቶች በመከሰት ላይ ያሉ ጥቃቶች፣ ስጋቶች እና ተጋላጭነቶች እንዴት መቀነስ እንደሚያስችሉ ግብአቶችን ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር የመጋራት እድል ሲኖራቸው፣ የመንግስት ባለድርሻ አካላት ደግሞ የብሄራዊ ደህንነት ሁኔታ ገጽታዎች ላይ በስለላም ሆነ በሳይበር ወንጀል መምሪያ የተገኘ መረጃን ጨምሮ ማወቅ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ መረጃ ይሰጣሉ።

#### 6.7.6.3.1. የትግበራ መምሪያ

- የመረጃ መጋራት ዘዴንና ዘዴውን የሚያስተዳድሩ መሰረታዊ መርሆችና ደንቦች በሚገባ መግለጽ(ለምሳሌ፦ መረጃን ይፋ ያለማድረግ ስምምነቶች፣ የመተማመኛ ደንቦች…ወዘተ)፤
- መረጃ ለመጋራት ዘርፉን መሰረት ያደረገ አካሄድ መከተል (ለምሳሌ፦ አንድ የመረጃ መጋሪያ ለኢንተርኔት አገልግሎት አቅራቢዎች፣ አንድ ለሃይል ማመንጫ፣…ወዘተ)፤ በሁሉም የመረጃ መጋሪያ ስርዓቶች መካከል በቂ የሆነ የመረጃ ፍሰት መኖሩን ማረጋገጥ)፤
- ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችና ቁልፍ ስጋቶች እና ተጋላጭነቶች ላይ ትኩረት ማድረግ (ለምሳሌ፦ ዋና/ቁልፍ መቋረጦች፣…)፤
- ባለድርሻ አካላት (በተለይ የግል ዘርፉ) ተሳትፎ እንዲያደርጉና ምስጢራዊ መረጃ እንዲያጋሩ ተገቢ የሆኑ ማበረታቻዎችን (የትንተናውን ውጤቶች መጋራት) ማቅረብ፤
- ትክክለኛ ገጽታ ያላቸው እና ትክክለኛ የሆኑ ልዩ ባለሙያዎች በስርዓቱ ላይ መሳተፋቸውን ማረጋገጥ፤ በተለምዶ ተሳታፊዎቹ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ልዩ ባለሙያዎች (ለምሳሌ፦ ዋና የኢንፎርሜሽን ደህንነት ኦፊሰሮች) ኢንፎርሜሽንን በኮርፖሬሽን ደረጃ መጋራት እንዲችሉ ማድረግ፤
- ልዩ ባለሙያዎች ከህግ አስፈጻሚ፣ ከስለላ፣ ከብሄራዊ/መንግስታዊ/CERTs እና ተፈላጊ የሆኑ ሬጉሌቶሪ አካላት መገኘት እንዳለባቸው መወሰን፤
- በልዩ ባለሙያዎች መካከል መተማመን እንዲያብብ የመረጃ መጋሪያ ስርዓትን መጠን ትንሽ ማድረግ፤
- ምስጢራዊ መረጃን ለመጋራት መደበኛ የሆኑ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት፤ መንግስት ሂደቱን ማሳለጥና የሎጂስቲክ ድጋፍ ማድረግ፤ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት የጋራ ኃላፊነት መሆኑን ለማሳየት ኢኒሽቲቩን መምራት፤
- የሳይበር ደህንነትን በከፍተኛ ደረጃ ለማስፋት ተገቢ የሆኑ የሃገራዊና ዓለም-አቀፍ የሚታመኑ የመረጃ መጋራት ኮሚዩኒቲዎችን መለየት እና የተሳትፎ ሁኔታን መወሰን፤
- የብሄራዊ አደጋ መዝገብን ወቅታዊ ማድረግ እና በቀድሞ ማስጠንቀቂያ ስርዓቶች ተገቢ ለሆኑና ኢላማ ለተደረጉ ተጠቃሚዎች ማንነትን ሳያሳውቁ የተሰበሰበውን መረጃ ማሰራጨት፤

## 7. የባለድርሻ አካላት ኃላፊነትና ሚና

ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የመረጃ መሰረተ ልማት ተቋማት ይህንን የፖሊሲና ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ መመሪያ የመተግበርና ተልዕኳቸውን መሰረት ያደረጉ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን ግዴታ አለባቸው። በተጨማሪ ከዚህ መመሪያ ዓለምአቀፍ ስታንዳርዶች ጋር የሚጣጣም የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች የመንደፍና የመተግበር ኃላፊነት አለባቸው።

### 7.1. ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ

1. የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራ በባለቤትነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤
2. የኢንፎርሜሽንና ቁልፍ የመሰረተ ልማቶች ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ብሔራዊ የፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ተፈፃሚነት ይከታተላል፤
3. መንግስታዊና የግል ተቋማት ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕቀፎችን ተከትለው የየራሳቸው ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀርጸው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍ ይሰጣል፤ አፈጻጸማቸውንም ይቆጣጠራል፤
4. የሳይበር ደህንነት ተልዕኮውን ለማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ዓለምአቀፋዊ ቅንጅትን ይፈጥራል፤
5. ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ደህንነት ዙሪያ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን በመቅረፅ ከሌሎች ጋር እየተባበረ አቅምን ይገነባል፤
6. ከመንግስትና ከግል ተቋማት፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የተወከሉ ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ምክርቤት ያቋቁማል፤ ይመራል፤
7. ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ የትግበራ መሪ እቅድ (መርሃ ግብር) በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፤
8. በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ መካከል የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የአጋርነት የአሰራር ስርዓቶች ይዘረጋል፤

### 7.2. የኢትዮ ሰርት (CER$^2$T)

1. በሀገር ደረጃ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ሁኔታዎችን ይተነትናል፣ ክትትል ያደርጋል፤
2. የሳይበር ደህንነት ክስተቶችንና ጥቃቶችን ይቆጣጠራል፤
3. የሳይበር ደህንነት ክስተቶችን ለመከላከል የሚያስችል አቅም ይፈጥራል፤
4. ከብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ምክር ቤት የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ይፈጽማል፤

### 7.3. ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ምክር ቤት(ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት አመራር ስርዓት)

1. የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የፖሊሲና ስትራቴጂው አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በማድረግ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
3. የፖሊሲና ስትራቴጂው ውጤታማነት በመገምገም ውሳኔ ያስተላልፋል፤ ጉድለቶች እንዲስተካከሉ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
4. የፖሊሲውንና ስትራቴጂውን አፈፃፀም መነሻ በማድረግ ለማሻሻል አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
5. በሳይበር ደህንነት ጉዳዮች ዙሪያ የመንግስት አማካሪ አካል ሆኖ ይሰራል፤
6. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የባለድርሻ አካላት ሚናና ኃላፊነቶች ይለያል፤ ይመራል፤ያስተባብራል፤

### 7.4. የህግ አካላት

1. የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነትና ስለላ ወንጀለኛን ይለያሉ፤ ይከላከላሉ፤ ይመረምራሉ፤
2. የሳይበር ወንጀል ሲፈፀም ተጠርጣሪውን ወደ ህግ ያቀርባሉ፤
3. የሳይበር ወንጀል የህግ ተጠያቂነት ያረጋግጣሉ፤ ውሳኔ ይሰጣሉ፤

### 7.5. የግሉ ዘርፍ

1. ለቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማት የሚውል የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎት በማቅረብ የበኩላቸውን ድርሻ ይወጣሉ፤

2. የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ እና የቴክኒካል ድጋፍ ይሰጣሉ፤
3. የሳይበር ጥቃቶችንና ስጋቶችን ለመቀነስና ለመከላከል የሚያስችሉ ምርቶችና አገልግሎቶች ያቀርባሉ፤
4. የሳይበር ደህንነት ምክርቤት አባል በመሆን በምክር ቤቱ የሚሰጣቸውን ኃላፊነትና ግዴታዎች ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

## 7.6.የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

1. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራትና ለማሳደግ የሚያስችል የትምህርትና ስልጠና መረሃ ግብሮችን ያዘጋጃሉ፤ ይሰጣሉ፤
2. አስተማማኝና ወጪ ቆጣቢ የሳይበር ደህንነት መፍትሄዎችን ለማመንጨትና ለማበለፀግ የሚያስችል ጥናትና ምርምር ያካሄዳሉ፤
3. የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ በሚደረጉ የምርምርና ልማት ተግባራት በግንባር ቀደምትነት ከሚሰሩ የቴክኖሎጂ ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሰራሉ፤
4. የሳይበር ደህንነት ምክር ቤት አባል በመሆን የሚሰጣቸውን ኃላፊነትና ግዴታዎች ይወጣሉ፤

## 7.7.ቁልፍ የመሰረተ-ልማት ዘርፎች

1. የቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነት ስጋቶችና ክስተቶች ይለያሉ፤ በቅደም ተከተል ያሰቀምጣሉ፤ ጥበቃ ያደርጋሉ፤
2. የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የዳሰሳ ጥናት ያደርጋሉ፤
3. የሳይበር ደህንነት ስጋቶች፣ ጥቃቶች እና ክስተቶች የመረጃ ልውውጥና ሪፖርት ያደርጋሉ፤

## 8. ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ የማስፈጸሚያ መርሃ ግብር

### የትኩረት አቅጣጫ 1፦የህግ እና ቁጥጥር ማዕቀፍ

| ግቦች | የማስፈጸሚያ ስልቶች | የሚመራው አካል | ተባባሪ አካል | የሚከናወንበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|
| የሳይበር ደህንነት ስጋቶችንና ተጋላጭነቶችን መቀነስ፤ ጥቃቶችን ለመከላከል እና ለመቋቋም የሚያግዙ፤ እንዲሁም ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸው ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ህጎች እና ስታንዳርዶች ጋር ተጣጣሚነት ያላቸው የሳይበር ደህንነት ሕግጋት እና ቁጥጥር ማዕቀፎችን ማውጣት፤ በቀጣይነትም ማሻሻል፤ | በመንግስት እና በቁልፍ የግል ተቋማት ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ስታንደርዶች እና የአሰራር ስርዓቶች መቅረጽ፣ መተግበር፤ | ✓ ኢመደኤ<br>✓ ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ም/ቤት | ✓ ፍትህ አካላት | ከ2013 ጀምሮ |
| | የሳይበር ደህንነት ሕግጋትና የቁጥጥር ማዕቀፎች ተቀባይነት እና ተፈፃሚነት ለማሳዳግ በሂደቱ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ እንዲሰራ ይደረጋል፤ | | | |
| የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ የሳይበር ስለላ እና መሰል ጥቃቶች ለመከላከል የሚያስችል የህግ አካላትን አቅም መገንባት፤ | የሳይበር ደህንነት ህጎችን ለማስፈጸም የመርማሪዎች፣ አቃቤ ህጎች፣ ዳኞች እና ሌሎች የፍትህ አካላት በትምህርት፣ በስልጠና፣ በምክክር መድረኮች፣ በኮንፈረንሶችና በመሳሰሉት ዘዴዎች አቅማቸው በቀጣይነት ይገነባል፤ | | | |
| በሀገር ውስጥ የሚመረቱና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የሳይበር ደህንነት ምርቶችና አገልግሎቶች፤ እንዲሁም ቁልፍ የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎች ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ፍላጎትን ያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፤ | በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ የሚገቡ የሳይበር ደህንነት ምርቶች ጥራትና ብቃታቸው ይፈተሻል፤ የፈጻሚ አካሉን በቀጣይነት የማብቃት ስራዎች ይሰራሉ፤ | ኢመደኤ | ✓ ሁሉም የመንግስት ተቋማት | ከ2013 ጀምሮ |
| ማህበረሰቡ በሀገሪቱ የሳይበር ደህንነት አቅሞች ዙሪያ ያለውን ዓመኔታ ለማሳደግ በኢንፎርሜሽን አሰባሰብ፣ ትንተና፣ ስርጭት፣ አጠቃቀም፣ ክምችት እና አወጋገድ ዙሪያ ደረጃቸውን የጠበቁ የህግና ቁጥጥር | ከሳይበር ደህንነት ህግጋትና ቁጥጥሮች ዙሪያ ማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረው የንቃተ-ህሊና ስራዎች ይሰራሉ፤ | ኢመደኤ | ✓ ፍትህ አካላት<br>✓ ሰላም ሚ/ር | ከ2013 ጀምሮ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ማዕቀፎችን መዘርጋት፤ | | | | |

ረቂቅ

## የትኩረት አቅጣጫ 2፦ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና

| ግቦች | የማስፈጸሚያ ስልቶች | የሚመራው አካል | ተባባሪ አካል | የሚከናወንበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|
| የመንግስት ተቋማት፣ የግል ተቋማትና ዜጎች በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ያላቸውን እውቀትና አመለካከት ማዳበር፤ | በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የተሰማሩ ተቋማት ተደራሽነታቸውን በማስፋትና በማጠናከር ለህብረተሰቡ የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ መስጠት፤ | ኢመደኤ | ✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት<br>✓ ከፍተኛ ት/ት ተቋማት<br>✓ ትምህርት ሚ/ር<br>✓ ኢትዮ ቴሌኮም | ከ2013 ጀምሮ |
| | በሳይበር ደህንነት ክስተቶች ዙሪያ ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚያስችሉ የጥሪ ማዕከልና ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራዎች ይሰራሉ፤ | | | |
| | በትምህርት ተቋማት የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ክበቦች ይቋቋማሉ፤ | | | |
| ከጥንቃቄ ጉድለትና ካለማወቅ የሚደርሱ የሳይበር ጥቃቶች፣ ስጋቶች እና ተጋላጭነቶችን መቀነስ፣ | በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የተሰማሩ ተቋማትን በማስፋትና በማጠናከር ለህብረተሰቡ ወቅታዊ የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ እንዲሰጡ ይደረጋል፤ | | ✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት<br>✓ ቁልፍ መሰረተ ልማት ያላቸው ተቋማት<br>✓ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት<br>✓ ትምህርት ሚ/ር | ከ2013 ጀምሮ |
| | በሀገሪቱ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ተቋማት በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ወቅታዊና ቀጣይነት ያለው የምክክር መድረኮች፣ ፓነሎች፣ ውይይቶች እና የመሳሰሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ይዘጋጃሉ፤ | | | |
| የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶችና ስጋቶች ለመቀነስ፤ እንዲሁም ጥቃቶች ለመከላከል የሚያስችል የዜጎች ንቃተ-ህሊና ማሳደግ እና ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ባህል መፍጠር፤ | ብሄራዊ የሳይበር ደህንነት ሳምንት በማክበር ሃገር አቀፍ የንቃተ-ህሊና ማጎልበቻ ዘመቻዎች ይከናወናሉ፤ | | | |
| | የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የህብረተሰቡ ንቃተ-ህሊና እና ግንዛቤ ለማሳደግ የተለያዩ ወቅታዊነታቸውን የጠበቁ የሳይበር ደህንነት ፕሮግራሞች ይዘጋጃሉ፤ ይቀርባሉ፤ | | ✓ የሚዲያ አካላት | ከ2013 ጀምሮ |
| | በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ለሚሰሩ ለመገናኛ ብዙሃን፣ ለግል ተቋማት፣ ለሲቪክ ማሕበራት እና ሌሎች አካላት እውቅና እና ማበረታቻ ይሰጣል፤ | | ✓ የሚዲያ አካላት<br>✓ ሲቪክ ማህበራት<br>✓ ቁልፍ የግል ተቋማት | |

## የትኩረት አቅጣጫ 3፦ የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ

| ግቦች | የማስፈጸሚያ ስልቶች | የሚመራው አካል | ተባባሪ አካል | የሚከናወንበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|
| የሳይበር ደህንነት ስጋት፣ ተጋላጭነት እና ጥቃት ለመለየት፣ ለመዳሰስ እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ተቋማዊ መዋቅሮችንና አቅሞችን መገንባት፤ | የሳይበር ደህንነት ትምህርት በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ውስጥ ይካተታል፣ | ✓ ኢመደኤ<br>✓ ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ም/ቤት | ✓ ትምህርት ሚ/ር<br>✓ ከፍተኛ ት/ት ተቋማት<br>✓ ሳይንስና ከፍተኛ ት/ት ሚ/ር | ከ2013 ጀምሮ |
| | የሳይበር ደህንነት አቅም ለማሳደግ የሚረዱ ወቅታዊ የሆኑ የትምህርትና ስልጠና ሰርትፊኬሽኖች ለባለሙያዎች ይሰጣል፤ | | | |
| | የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችን ሊያሰራ የሚችል የብቃት መመዘኛ ስታንዳርድ ማስቀመጥ፤ | | | |
| የመንግስት፣ የግል እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሳይበር ደህንነት አቅማቸውን ማጠናከር፤ | የመንግስትና የግል ተቋማት እንዳስፈላጊነቱ የሳይበር ደህንነት የአሰራር ስርዓቶች ይተገበራሉ፤ | | ✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት | ከ2013 ጀምሮ |
| | በመንግስት፣ በግልና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የምርጥ ተሞክሮ፣ የልምድ ልውውጥና፣ የእውቀት ሽግግር ለማድረግ የሚያስችሉ መድረኮች ይዘጋጃሉ፤ | | ✓ ትምህርት ሚ/ር<br>✓ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት(የመንግስት እና የግል)<br>✓ የምርምር ተቋማት | |
| በሀገር ደረጃ ብቃት ያላቸው የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችን መፍጠር፤ | በቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ተቋማት ውስጥ በሚሰሩ ባለሙያዎች ስብዕና ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት የምልመላ እና የማብቃት ስራ ይሰራል፤ | | ✓ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት(የመንግስት እና የግል)<br>✓ የሚዲያ አካላት | ከ2013 ጀምሮ |
| | በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በዘርፉ ከተሰማሩ ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር የልምድ ልውውጥ እና የእውቀት ሽግግር ይደረጋል፤ | | ✓ የሚዲያ አካላት<br>✓ ቁልፍ የግል ተቋማት | |

## የትኩረት አቅጣጫ 4፦ የሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት

| ግቦች | የማስፈጸሚያ ስልቶች | የሚመራው አካል | ተባባሪ አካል | የሚከናወንበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|
| ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ምርቶችና አገልግሎቶች በምርምርና ልማት ላይ የተመሰረቱ ማድረግ፤ | ቁልፍ የመሰረተ ልማቶች ከጥቃት መከላከል የሚያስችሉ በጥናት እና ምርምር የተለዩ ሀገራዊ አሻራ ያላቸው አስፈላጊ ቴክኖሎጂዎች ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ይደረጋል፤ | ✓ ኢ.መደኤ<br>✓ ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ም/ቤት | ✓ የከፍተኛ ት/ት ተቋማት<br>✓ ሳይንስ እና ኢኖቬሽን ሚኒስቴር | ከ2013 ጀምሮ |
| | አዳዲስ ምርት እና አገልግሎቶች በዘርፉ እንዲበራከቱ የሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት ለማጠናከር የተለያዩ ማበረታቻዎች ይሰጣሉ፤ | | | |
| የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶች፣ ስጋቶች እና ጥቃቶች መንስዔዎቻቸውን በጥናትና ምርምር መለየት፤ መፍትሄዎች ማቅረብ፤ | የምርምርና ልማት ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል እውቀት፣ ክህሎት፣ ልምድ እና የቴክኖሎጂ አቅም ይገነባል፤ | | ✓ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት(የመንግስት እና የግል)<br>✓ የምርምር ተቋማት<br>✓ የደህንነት ተቋማት<br>✓ ሳይንስ እና ኢኖቬሽን ሚኒስቴር | ከ2013 ጀምሮ |
| | በተለያዩ የምርምር ተቋማት፣ የደህንነት ተቋማት እና ዩኒቨርሲቲዎች የሳይበር ደህንነት እንዳስፈላጊነቱ የልህቀት ማዕከላት ይቋቋማል፤ | | | |
| | በሳይበር ምህዳር ውስጥ ባሉ ተዋናዮች መካከል ያለው ትብብር በማጠናከር የተቀናጀ የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ወቅታዊነታቸውን የጠበቁ የእውቀትና የልምድ ልውውጥ መድረኮች፣ ኮንፈረንሶችና ፕሮግራሞች ይካሄዳሉ፤ | | | |
| የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ ሃገር በቀል ዕውቀት እና ፈጠራዎችን መሰረት ያደረገ የምርምር እና ልማት አቅም መገንባት፤ | የሳይበር ደህንነት የምርምር እና ልማት ተግባራትን ከሚመለከታቸው የመንግስትና የግል ተቋማት እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ይፈጸማል፤ | | ✓ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት(የመንግስት እና የግል)<br>✓ የምርምር ተቋማት<br>✓ ሳይንስ እና ኢኖቬሽን ሚኒስቴር | |
| | ብሄራዊ የምርምርና ልማት ፍኖተ-ካርታ ለሳይበር ደህንነት በማዘጋጀት ይሰራል፤ | | | |
| | ምርምር እና ፈጠራ የሚያበረታቱ የሳይበር ደህንነት ጋር የተያያዙ ፕሮግራሞችን ይቀረፃሉ፤ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ እና የተቀናጀ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት ባህል መገንባት፤ | የግል ሴክተሩ በአገሪቱ  የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት ፕሮግራሞች እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤ | ✓ ኢመደኤ | ✓ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት(የመንግስት እና የግል)<br>✓ ቁልፍ መሰረተ ልማት ያላቸው ተቋማት<br>✓ የምርምር ተቋማት<br>✓ ሳይንስ እና ከፍተኛ ት/ት ሚ/ር | ከ2012 ጀምሮ |
| | ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶችን ተጋላጭነትና ጥቃት ለመከላከል በሚያስችል ሁኔታ በቀጣይነት በምርምርና ልማት ይደገፋል፤ | | | |
| | በብሄራዊ ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ በሳይበር ደህንነት ጉዳዮች ዙሪያ ልዩ ትኩረት በመስጠት የምርምር እና የልማት ተግባራት ይከናወናሉ፤ | | | |
| | በሃገሪቱ ለስጋት ሀይሎች ጥቃት የማይበገር የሳይበር ክልል እንዲኖር ጠንካራ የሆነ የሳይበር ደህንነት እንዱስትሪ ለመገንባት በጥናትና ምርምር ይደገፋል፤ | | | |

## የትኩረት አቅጣጫ 5፦ ዲጂታል ማንነት እና ግላዊ መረጃ ጥበቃ

| ግቦች | የማስፈጸሚያ ስልቶች | የሚመራው አካል | ተባባሪ አካል | የሚከናወንበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|
| በዜጎች ዘንድ ታዓማኒነት ያለው የዲጂታል አገልግሎት እና ግላዊ መረጃ ጥበቃ እንዲኖር ማድረግ፤ | የግላዊ መረጃ ደህንነት ማረጋገጥ የሚያስቸሉ አቅሞች፣ ተቋማዊ ማዕቀፎች፣ የህግ እና የቁጥጥር አሰራር ስርዓቶች በቅንጅት ተግባራዊ ይደረጋል፤ | ✓ ኢመደኤ<br>✓ ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ም/ቤት | ✓ ፌደራል ፍርድ ቤት<br>✓ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን<br>✓ ፍትህ አካላት | ከ2013 ጀምሮ |
| | አስተማማኝ የሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂ እና ገለልተኛ የዳታ ፕራይቪሲ ህግ ማስተዋወቅ፣ ህጋዊ የመረጃ አሰባሰብ አሰራር እና መቆጣጠርያ መመሪያ ይዘጋጃል፤ | | | |
| | በግላዊ መረጃ ጥበቃ እና በሳይበር ደህንነት ማረጋገጥ መከካል ያሉ ተቃርኖዎችን ለማስታረቅ የሚያስችሉ አሰራሮች ይተገበራሉ፤ | | | |
| | የግለሰቦች መረጃ የሚሰበስቡ፣ ፕሮሰስ የሚያደርጉ እና የሚያከማቹ ተቋማትምንዓይነትኢንፎርሜሽን፣ከማን፣ እንዴትመሰብሰብ፣ፕሮሰስማድረግ፣መጠቀም፣ማከማቸት፣ እናማስወገድእንዳለባቸው በየጊዜው የማንቃት ስራ ይሰራል፣ | | ✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት<br>✓ የፍትህ አካላት | ከ2012 ጀምሮ |
| | መንግስታዊያልሆኑተቋማትበልዩሁኔታየግለሰቦችንግላዊነት መብት መጠበቅየሚያስችልአሰራርበሚያወጧቸውየሳይበርደህንነትህጎች፣ መመሪያዎች፣ደንቦችእናሌሎችየአሰራርስርዓቶችእንዲካተቱ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፡ | | | |
| | የሚመለከታቸው ተቋማት የዜጎችን ግላዊመረጃ በተመለከተ በቀጣይነት ክትትል እናየትንተናስራተግባራዊ ይደረጋል፤ | | | |
| | ኤሌክትሮኒክ የመንግስት አገልግሎቶች ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ይደረጋል፤ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ሃገሪቱ በዲጂታል ግላዊ መረጃ አጠባበቅ ዙሪያ ያላትን ክፍተት ለመሙላት ከዓለም አቀፍየግለሰብ መረጃ ስምምነቶች፣ ከህግማዕቀፎችና ፖሊሲዎች ጋር የተጣጣመ የአሰራር ስርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፤ | ✓ ኢ.መደኤ<br>✓ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር | ✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት<br>✓ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር | |
| ማንነትን መሰረት ያደረጉ በዲጂታል የሚፈጸሙ የሃይማኖት ጽንፈኝነት፣ የብሄር ተኮር ጥቃቶችንና የመሳሰሉትን መግታትና መከላከል፤ | የዲጂታል የጥላቻ ንግግር፣ ፅሁፍ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የሚከለክል፣ አግባብነት ያለው የሳይበር አጠቃቀም የሚያበረታታ ደንቦችና አሰራር ስርዓት ይተገበራል፤ | ✓ ኢ.መደኤ<br>✓ ሰላም ሚ/ር | ✓ የፍትህ አካላት<br>✓ የሚዲያ አካላት<br>✓ ሰላም ሚ/ር<br>✓ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት(የመንግስት እና የግል)<br>✓ ትምህርት ሚ/ር<br>✓ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን | 2013 ጀምሮ |
| በታዳጊዎች ላይ የሚደርሱ የሳይበር ስጋቶችን፣ ተጋላጭነቶችንና ጥቃቶችን መከላከል፤ በኢትዮጵያ ማህበረሰብ እሴቶችና በመልካም ስብዕና ታንፀው እንዲያድጉ ሳይበር ሊጫወተው የሚገባ ገንቢ ሚና ማሳደግ፤ | የታዳጊዎች የዲጂታል መብት ጥሰት መከላከል የሚያስችል የክትትል አቅም እንዲኖር ይሰራል፣<br>ተቋማት በአወቃቀራቸው የታዳጊዎች ዲጂታል መብት እውቅና የሰጠ አወቃቀር እንዲኖራቸው ይሰራል፣ | | | |
| በሳይበር ምህዳር ላይ የሚደርስ ጾታዊ ጥቃት፣ ወሲባዊ ትንኮሳ፣ የሥነ-ልቦና ተፅዕኖ መከላከል እና መቀነስ፤ | በታዳጊዎችና ሴቶች የዲጂታል ማንነትና ግላዊ መረጃ ጥበቃ ለማጠናከር ማህበረሰቡን ያሳተፈ ህዝባዊ ንቅናቄዎች በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን፣ መድረኮች፣ ኮንፍረንሶች እና ወርክሾፖች ይዘጋጃሉ፤<br>የሳይበርግላዊነትደህንነትአስፈላጊነትላይእውቅናየሚሰጡሰፋፊየምክክርመድረኮችይመቻቻሉ፡ | ✓ ኢ.መደኤ<br>✓ ሴቶች፣ ወጣቶች እና ህጻናት ሚ/ር | ✓ ሁሉም የመንግስት ተቋማት<br>✓ ሁሉም መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት<br>✓ የፍትህ አካላት | |

## የትኩረት አቅጣጫ 6፦ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶች ጥበቃ

| ግቦች | የማስፈጸሚያ ስልቶች | የሚመራው አካል | ተባባሪ አካል | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ |
|---|---|---|---|---|
| ቁልፍ መሰረተ-ልማቶች እና ተቋማት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶች፣ ጥቃቶችና ውድመቶችን የመለየት፣ የመከላከል እና ምላሽ የመስጠት አቅም ማጎልበት፤ | ቁልፍ የመንግስትና የግል ተቋማትን ሳይበር ደህንነት ሊያስጠብቅ የሚችል የተቀናጀ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ፡፡ | ✓ ኢመደኤ<br>✓ የሳይበር ደህንነት ም/ቤት | ✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት<br>✓ የፍትህ አካላት | 2013 ጀምሮ |
| | ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችንና ሊደርሱባቸው የሚችሉትን ጥቃቶችን የሚለይና አፋጣኝ መልስ የሚሰጥ አካል ይቋቋማል፤ ተቋሙን የሚያጠናክሩ የአሰራር ስርዓቶች እና አቅጣጫዎች ይዘረጋሉ፤ | | | |
| | ብሔራዊ የቁልፍ መሰረተ-ልማቶች ደህንነት አመራር ስርዓት ይዘጋጃል፤ ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ በቀጣይነት ይሻሻላል፤ | | | |
| | ቁልፍ መሰረተ-ልማቶችን ለመጠበቅ የመንግስት እና የግል ተቋማት ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁና ሀገራዊ አውድ ያገናዘቡ የሳይበር ደህንነት ሕግጋት፣ ፖሊሲዎች፣ ስታንዳርዶችና፣ ማዕቀፎች ስራ ላይ ይውላሉ፤ | | | |
| | ቁልፍየኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማት ተቋማት ዓለም-አቀፍ ይዘት ካላቸው የኢንፎርሜሽን ደህንነት ስታንዳርዶችና የአሰራር ሥርዓቶች ጋር የተጣጣመ መርሃ-ግብሮች እንዲቀርፁና የስራ ሂደቶቻቸው አካል እንዲያደርጉ ይደረጋል፤ | | | |
| | ለሚመለከታቸው አካላት በቁልፍ መሰረተ-ልማቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶች፣ ጥቃቶችና ውድመቶችን ለመለየት፣ ለመቀነስ፣ ለመከላከል እና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ወቅታዊነታቸውን የጠበቁ ትምህርቶች፣ ስልጠናዎች፣ የምክክር መድረኮች እና የመሳሰሉት ይዘጋጃል፤ ይሰጣል፤ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ለቁልፍ መሰረተ-ልማቶች የሚውሉ ሀገር በቀል የኢኮቴ ምርቶችን የማምረት አቅም ይገነባል፤ | | | |
| ከውጭ የሚገቡ እና በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማት ምርቶችና አገልግሎቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፤ | ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶች፣ የኢኮቴ ምርቶች እና አገልግሎቶች ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ደህንነት ቴክኒካዊ ስታንዳርዶች ስራ ላይ ይውላል፤ | ኢ.መደኤ | ✓ ሳይንስና ኢኖቬሽን ሚ/ር<br>✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት | |
| | በማንኛውም ጊዜ የተጋላጭነት ፍተሻና የኢንፎርሜሽንና የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማት የደህንነት ኦዲት እንዲካሄድና ፈጣን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ይደረጋል፤ | | | |
| ለቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶች ልዩ ጥበቃ ለማድረግ የመንግስት እና የግል ዘርፍ ትብብር እና ቅንጅት መፍጠር፤ | ለቁልፍ መሰረተ ልማቶችና ስርዓቶች 24/7 አካላዊና ምናባዊ ጥበቃ ይደረጋል፤ | | ✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት<br>✓ ሚዲያ አካላት<br>✓ ጸጥታ አካላት | 2013 ጀምሮ |
| | ለቁልፍ መሰረተ-ልማቶች ልዩ ጥበቃ ለማድረግ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተግባራትና ኃላፊነቶች በመለየት ይሰጣል፤ | | | |

## የትኩረት አቅጣጫ 7.1 ፦ሃገራዊ ቅንጅት እና አጋርነት

| ግቦች | የማስፈጸሚያ ስልቶች | የሚመራው አካል | ተባባሪ አካል | የሚከናወንበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|
| ሀገራዊ ሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ በመንግስት፣ በግሉ ዘርፍ እና በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅትና አጋርነት መመስረትና ማጠናከር፤ | የሳይበር ደህንነት ቅንጅት እና አጋርነት የሚመራ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ይደረጋል፤ | ✓ ኢ.መደኤ<br>✓ ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ም/ቤት | ✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት | ከ2013 ጀምሮ |
| | ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ፎረም ይቋቋማል፤ | | | |
| | በሀገር ደረጃ የሳይበር ደህንነት ኮንፈረንሶች፣ ሴሚናሮችና መሰል ቅንጅትን የሚያጠናክሩ መርሃ ግብሮች በየጊዜው ይዘጋጃሉ:: | | | |
| | በባለድርሻ አካላት ዘንድ የድርሻና ኃላፊነት ግልጽነት ይፈጠራል፤ | | ✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት<br>✓ የፍትህ አካላት<br>✓ ዜጎች<br>✓ ሲቪክ ማህበራት | ከ2013 ጀምሮ |
| | የሳይበር ደህንነት ባለድርሻ አካላት መካከል የልምድ ልውውጥና የዕውቀት ሽግግር ስርዓት ይዘረጋል፤ | | | |
| | የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት ድንገተኛ የኮምፒውተር አደጋዎች መከላከል ክፍል እንዲኖራቸውና በክስተቶች ዙሪያ የልምድ ልውውጥ እንዲኖር ይደረጋል፤ | ኢ.መደኤ (ኢትዮ ሰርት) | ✓ ሳይንስና ኢኖቬሽን ሚ/ር<br>✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት | |
| | የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት ድንገተኛ የኮምፒውተር አደጋዎች መከታተያ ሥርዓታቸው ከብሄራዊ የኮምፒውተር አደጋዎች መከታተያ ሥርዓት ጋር የተቀናጀ እና የሚመጋገብ ይደረጋል:: | | | |
| የሳይበር ደህንነት ምርት በማምረትና አገልግሎት በማቅረብ ላይ የተሰማሩ ሀገር በቀል የግል ተቋማት እንዲጨምሩና እንዲጠናከሩ በማድረግ የሀገሪቱን የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎት ፍላጎት ከማርካት አልፈው በዓለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ | አዳዲስ ተቋማት እንዲፈጠሩና ያሉት ተቋማት እንዲጠናከሩ የሚያግዝ መርሃ ግብሮች ይቀረጻሉ፤ ተግባራዊ ይደረጋሉ፤ | ኢ.መደኤ | ✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት<br>✓ ሚዲያ አካላት<br>✓ ጸጥታ አካላት | ከ2013 ጀምሮ |
| | ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚውሉ የሳይበር ደህንነት ውጤቶችን ለሚያመርቱ ተቋማት ድጋፍ ይደረጋል፤ | | | |
| | ደረጃቸውን የጠበቁ የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎቶች በሀገሪቱ ገበያ ቅድሚያ ማግኘት የሚችሉበት ድጋፍ ይመቻቻል፤ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ማስቻል፤ | በዓለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያግዝ ድጋፍ ይደረጋል፤ | | | |

| ግቦች | የማስፈጸሚያ ስልቶች | የሚመራው | ተባባሪ አካል | የሚከናወንበት |
|---|---|---|---|---|

**የትኩረት አቅጣጫ 7.2፦ዓለም አቀፍ ትብብር**

| | | አካል | | የጊዜ ሰሌዳ |
|---|---|---|---|---|
| የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ ስለላ እና መሰል ዓለም-አቀፍ ይዘት ያላቸው የሳይበር ደህንነት ስጋቶች ለመከላከል ትብብር መፍጠር፤ | በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የሚኖሩ ዓለም-አቀፋዊ የትብብርና የአጋርነት ስምምነቶች እንደ አስፈላጊነታቸው ይፈረማል፤ | ✓ ኢ.መደኤ<br>✓ ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ም/ቤት | ✓ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር<br>✓ የፍትህ አካላት<br>✓ ሰላም ሚ/ር<br>✓ የተለያዩ በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የተሰማሩ ዓለም አቀፍ<br>✓ ኢንተር ፖል | ከ2013 ጀምሮ |
| | የሳይበር ጥቃቶችን ለመመከት ከተለያዩ ሀገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረግባቸው መንገዶች ይመቻቻል፤ | | | |
| | ድንበር ተሻጋሪ የሳይበር ወንጀሎች፣ ሽብርተኝነቶች፣ ስለላና መሰል ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ በሃገራት መካከል የመረጃ ልውውጥ እና የቴክኒካል ድጋፎች ይደረጋሉ፤ | | | |
| በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የሚደረግ ዓለም አቀፍ ትብብር የሃገሪቱ የውጪ ጉዳይ ዲፕሎማሲ አካል እንዲሆን ማድረግ፤ | የሳይበር ደህንነትን የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ አካል ሆኖ እንዲሰራበት ይደረጋል፤ | ✓ ኢ.መደኤ | ✓ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር<br>✓ የፍትህ አካላት<br>✓ አለም አቀፍ የሳይበር ደህንነት ዙሪያ የተሰማሩ ተቋማት | ከ2013 ጀምሮ |
| | ዓለም-አቀፍ በሆኑ የሳይበር ደህንነት ትብብር መድረኮች ላይ ንቁ ተሳትፎ ይደረጋል፤ | | | |
| ሁለትዮሽና ከዚያ በላይ የሆኑ የሳይበር ደህንነት ስምምነቶችን ማበረታት እና ማጎልበት፤ | በሳይበር ደህንነት ጉዳዮች ላይ ብቃት ያላቸውን የሰው ኃይል ለመፍጠር ዓለም አቀፍ ስልጠናዎች ይመቻቻል፤ | ✓ ኢ.መደኤ<br>✓ ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ም/ቤት | ✓ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር<br>✓ ሳይንስና ኢኖቬሽን ሚ/ር<br>✓ ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት<br>✓ አለም አቀፍ የሳይበር ደህንነት ዙሪያ የተሰማሩ ተቋማት | |
| | የግልና የመንግስት ተቋማት ከሌሎች ሀገራት መንግስታትና የግል ተቋማት ጋር ያላቸውን የሳይበር ደህንነት ቁርኝት ተገቢ በሆነ መልኩ እንዲያጠናክሩ ሁኔታዎች ይመቻቻል፤ | | | |
| | የሳይበር ደህንነት ትብብር ለመፍጠር የሚያስችል ሃገራዊ አቅም ይገነባል፤ | | | |